እንደገና አዲስ ኪዳኑን ገለጠና ገደኛ ወይም ዕድለኛ ይሆናል ብሎ ባሰበበት ቦታ ያንኑ የጣት ጥቆማ ደገመ። የአሁኑ ቦታ ደግሞ ዮሐ. 13፥27 ነው። ቃሉም፥ 'የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ' የሚል ነበር። ይህ የዋኅ ሰው ምን ማድረግ ሊኖርበት ነው? በቶሎ መታነቅ? መጽሐፍ ቅዱስን በቂልነት ስለ እኛ የማይናገረውን እንደሚናገር በማሰብ ማንበብና ለመተግበር መጣር ወደ አደጋ እንደሚጥል ምሳሌው ሊያስተምረን ይችላል።

ቀድሞ ያወቅነው የለመድነው ነገር በእውነት ምክንያት፥ ማለትም፥ እውነትን በማወቃችን ምክንያት የሚለወጥ ከሆነ ሳንከፋ እውነትን መቀበል አለብን። የኛ ስሜትና አመለካከት ሁሌ እውነት ላይሆን ይችላል፤ ቃሉ ግን ሁሌም እውነት ነው። ያወቅነው እውነት አመለካከታችንን የሚለውጥ እንኳ ቢሆን ለዚያ እውነት መሸነፍ አለብን። ስሜት ተገቢ ቦታ ቢኖረውም የሰው ስሜት ብቻ ከተሰበከ እውነትን በትክክለኛ መልኩ ለማየት ያዳግታል። ከሰባኪ ስብከት ወደ ራስ የተመቻቸ አባባል መዝለል ደግሞ ከባድ አይደለም። ለምሳሌ በጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ መቅድመ ዓመታት፥ 'ሙሉ ወይም ፍጹም ቅድስና በምድር ላይ ሳለን የምናገኘው ወይም የምንቀዳጀው ነገር ነው፤ እያንዳንዱ የሰውነታችን ብልትም በቅድስና ኃይል ከኃጢአት ይነጻል' የሚል ትምህርት ነበረ። በንቅናቄው መጀመሪያ ደግሞ ከቀደምት መሪዎቹ አንዱ ቻርልስ ፓርሃም፥ 'እያንዳንዱ የሰውነታችን ብልት ከበሽታ ይነጻል' በሚለው ተካው። ከመንፈሳዊ መንጻት ወደ ሥጋዊ ፈውስ የተደረሰበት ሂደት ጊዜ የወሰደም አስቸጋሪም አልነበረም።

አንዳንድ አተረጓጎሞች ደግሞ ወደ አንድ ግብ ለመድረስ ብቻ ተብለው የተፈጠሩ ወይም የተሠሩ ናቸው። ኤሚ መክፈርሰን The Four Square Church የተባለውን ጴንጤቆስጣዊ ማኅበር የመሠረተች ሴት ናት። የስያሜውን ጽንሰ አሳብ ያገኘችው ሕዝ. 1፥1-28ን ስታስተምር ነበር። በምዕራፉ አራት ፍጡራን ይገኛሉ፤ ሰው፥ አንበሳ፥ በሬና ንስር። ሴቲቱ እኒህን ምስሎች እንዲህ በማለት ተረጎመቻቸው፤ ሰው ደኅንነት ነው፤ አንበሳ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን መናገር ነው፤ በሬ መለኮታዊ ፈውስ ነው፤ ንስር ደግሞ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። ፎር ስኳር ቤተ ክርስቲያን እንደ ስሙና እንደ አራቱ ማእዘናቱ እነዚህን አራት ዋና ዋና ነገሮች የሚሰብክ ቤተ ክርስቲያን ነው በማለት ጀመረች።[11] ይህን የመሰለው አተረጓጎም በዘመናችንና በአካባቢያችን ያልተለመደ አይደለም። ይህን የመሰለ ስሕተት እንዳይፈጸም ነው ሰባኪዎቻችን ጠንቃቃ ፈቺዎችና ገላጭ ሰባኪዎች ሊሆኑ የተገባው።

---

[11] Synan, p. 201.





ዛሬ የቃሉ ወተት በውኃ ቀጥኖ የወተቱ መልክ ንጣት መቅጠኑን ሳያሳውቅ እየጠጣነው እንገኛለን። ስናጣጥመው መቅጠኑን ባወቅን ነበር። ግን ወይ በውክቢያና ባለማስተዋል፥ ያለዚያም በወተቱ ብዙ ሰው ሠራሽ ስኳሮች ተጨምረውበት የወተቱ ውፍረት በጣዕም ተለውጦ ሳናውቀው እንጋተዋለን። መንፈሳዊ ምግብነቱ እየጠፋብን ነው። ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ስሕተት የስነ አፈታት ችግር ነው። ቀጥሎ ባሉት ገጾች ውስጥ በስፋትና በጥልቀትም ባይሆን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያየ የጽሑፍ ዓይነት ስንመለከት ማወቅ ያለብንን ዋና ዋና ነጥቦች እናያለን። በብሉይ ኪዳን የኦሪትን፥ የታሪክን፥ የቅኔያትንና የትንቢትን መጻሕፍት፤ በአዲስ ኪዳን ደግሞ የታሪክን፥ ማለትም፥ ወንጌላትንና የሐዋርያት ሥራን፥ የመልእክቶችንና የትንቢትን መጻሕፍት ባሕርያት እንመለከታለን። ባህርያታቸውን ብቻ ሳይሆን እነዚህን መጻሕፍት ስንተረጉም መከተልና መጠንቀቅ ያለብንን ዋና ዋና አሳቦችም አያይዘን እናያለን። እንደ መግቢያና መነሻ ግን ስለ ዳራ እንዲሁም ስለምናነብበው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጥቂት ነገሮችን ማለት ያስፈልጋል።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለአፈታኤ መሠረታዊ መነሻ ነው። ትርጉም ሲባል የተጻፈውንና የምናነብበውን ከመሠረታዊዎቹ ቋንቋዎች የተመለሰውን መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው። ቢቻል የመጀመሪያዎቹን ቃሉ የተጻፈባቸውን ቋንቋዎች ማወቁ ትልቅ ዕድል ነው። ካልሆነም ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሶች ወይም ትርጉሞች መጠቀም ቃሉን ለሚመረምር ጥቅም አለው። ይህ በአንድ ቋንቋ የተተረጎሙ የተለያዩ ትርጉሞች ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችም ሊሆን ይችላል። እንዲህ ማድረግ ምናልባት የሚያደናግርና ግርታ የሚፈጥር ይመስላል። ይሁን እንጂ ለአንድ አስተማሪ ወይም ሰባኪ ወይም ቃሉን በግል ለሚያጠና አማኝ ከአንድ በላይ ትርጉም መጠቀም ይበልጥ እንዲያጠናና አንዱን ከሌላው በማስተያየት ወደ ትክክለኛው አሳብ እንዲመጣ ይረዳዋል። ለጥናት አንድ ዋና ትርጉምን መምረጥ ግን አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ሲጻፍ በዕብራይስጥ፥ በአራማይስጥ ወይም ሱርስጥ እና በግሪክ ቋንቋዎች ነው። እነዚህን ቋንቋዎች ማወቅ ቃሉን ለመረዳት በጣም ጠቃሚ ነገር ቢሆንም ቃለ አምላክን ለመረዳት የግድ እነዚህን ቋንቋዎች ማወቅ አለብን ማለት አይደለም። እንዲህ ካልሆነ በተተረጎሙ መጽሐፍ ቅዱሶች መደገፍ ይኖርብናል ማለት ነው። ስለዚህ የምንጠቀመው መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ ትርጉም ወይም ከአንድ በላይ ቋንቋ ቢሆን ይመረጣል። ከአንድ በላይ ትርጉሞችን መጠቀም ቃላትን በግልጥ እንድንረዳ ይረዳናል።

ለምሳሌ፥ በአማርኛ በአንድ ዓይነት ፊደላት ተጽፈው በመጥበቅና በመላላት ብቻ የተለያዩ ትርጉሞች የሚሰጡ በጣም ብዙ ቃላት ይገኛሉ። በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ማጥበቅና ማላላት በተለይ የግስ አድራጊና ተደራጊ ለውጦችን ሊፈጥር ይችላል። ሆሴ. 5፥14 ያለው 'የሚያድንም'፥ ማቴ. 11፥12 ላይ ያለው 'ትገፋለች'፥ ወይም 1ቆሮ. 11፥27 እና 29 ላይ ያሉት 'ሳይገባው' የሚሉት ቃላት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ከአንድ በላይ ትርጉሞች ወይም ቋንቋ መጠቀም የቃሉ አሳብ የትኛው መሆኑን በቀላሉ ያሳውቀናል።

የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ሲተረጎም እንደምን እንደተተረጎመና በምን ሂደት ውስጥ ማለፉን ማወቅ ጠቃሚ ነገር ነው። ምን ያህል ጊዜ መፍጀቱ፥ በእንዴት የመሰሉ ሊቃውንት ተጠንቶ መሠራቱ፥ ለመጀመሪያው ቋንቋና አሳብ ምን ያህል የተጠጋ መሆኑ፥ የቃላቱ እኩያ ልዋጭ እንደምን መቀመራቸው፥ ትርጉሙ ከመጀመሪያዎቹ ቋንቋዎች ወይም ከሌላ አንድ መካከለኛ ቋንቋ መወሰዱ፥ ሌሎችም መሠረታዊ ነጥቦች በትርጉም ሂደት ውስጥ መካተታቸውን ማወቅ የተተረጎመው የእግዚአብሔር ቃል በእርግጥም የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ እንድንታመን ያደርገናል። በዚህ የትርጉም ሂደት ውስጥ ደግሞ ሐስዮተ ጽሑፋትና ሐስዮተ ልሳናት (textual criticism and linguistic criticism) ተገቢ ሚና ቸውን ማጣት የለባቸውም። እነዚህ የዋና ጽሑፎችና የተተረጎመው ትርጉም ውጪያዊና ውስጣዊ ተመሳሳይነትን እንዲሁም የዋናውን ቋንቋና የተቀባዩን ወይም የተተርጓሚውን ቋንቋ የቃላት ምጠና የሚያጠናና የሚመለከት ሥራ ነው። በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ያለው ታሪካዊና ባህላዊ ርቀትም አብሮ ይታያል።

ትርጉም በራሱ ሰፊ የጥናት መስክ ቢሆንም የመጽሐፍ ቅዱስን የጽሑፍ ትርጉም ሥራ በተመለከተ የትርጉም ንድፈ አሳብ የሚመደብባቸውን ሦስት መደቦች በአጭሩ እንመልከት።

አንደኛው ቃል በቃል ትርጉም (literal translation) የሚባለው ነው። በዚህ አተረጓጎም ታሪካዊ ርቀቱ እንደተጠበቀ ይቆያል። ቃሉ፥ ሐረጉ፥ ዐረፍተ ነገሩ ሳይቀር እንዳለ ከዋናው ቋንቋ አቀማመጥ ሳይዛባ ይተረጎማል። ይህ አተረጓጎም ከተቀባዩ ቋንቋ ይልቅ ለዋናው ቋንቋ ጠበቃ ይሆናል። እንዲህ ሲተረጎም አነባበቡና አሳቡ በተቀባዩ ቋንቋ ግር የሚል ሊመስልና ሊሆን ይችላል። በእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በመጀመሪያ የታተመው የ1878 ዓመተ ምሕረቱ የአማርኛው ትርጉም ይህን የአተረጓጎም ስልት የተከተለ ነው።

ሁለተኛው አኪል ልዋጭ ወይም እኩያ ልዋጭ (dynamic equivalent) የሚባለው ነው። ይህ ቃልን፥ ሐረግን ወይም ዐረፍተ ነገርን ከዋናው ቋንቋ ተቀብሎ እኩያ ወይም አቻ በሆኑ የተቀባዩ ቋንቋ ቃላትና ሐረጎች እንዲሁም ዐረፍተ ነገሮች ይለውጣል።





የዚህ ትርጉም የቋንቋው ፍሰትም በአንባቢው ዘንድ ግርታን የማይፈጥርና የተለመደ ዘዬን የተከተለ ስልት ነው። ይህ በትርጉም ሊቃናት ዘንድ እንደ ትክክለኛ ትርጉም ንድፈ አሳብ የሚወሰድ ስልት ነው። በመካከል ለጥቂት ጊዜ ከመቋረጥ ጋር በ1910 ተጀምሮ እስከ 1944 ዓመተ ምሕረት ከ30 ዓመታት በላይ ፈጅቶ ሲሠራ የቆየውና በ1954 የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ስልት የተከተለ መሆኑ በስፋት ይታያል።

ሦስተኛው ነፃ ትርጉም (free translation) የሚባለው ነው። ይህ የአተረጓጎም ስልት ከዋናው ቋንቋ ከቃላት ይልቅ አሳብን ብቻ ይወስድና በተቀባዩ ቋንቋ በዘመኑ በሚነገርበት ሁኔታ ተርጉሞ ይጽፈዋል። ይህ የትርጉም ስልት ደግሞ ከዋናው ቋንቋ ይልቅ ለተቀባዩ የሚጠነቀቅ ነው። 'ሕያው ቃል' የተባለው የአማርኛ ትርጉም ይህን የትርጉም ስልት የተከተለ ነው። ትርጉሞች ሲተረጎሙ እንጂ ሲመነዘሩ ማሳሳታቸው አይቀርም። አንድዳንድ ነጻ ትርጉሞች ክብደትን፥ ገንዘብን፥ ርዝመትንና ርቀትን ሌሎችንም መለኪያዎች እንደነበሩ ከመተርጎም ይልቅ በዚህ አገርና በዚህ ዘመን መለኪያ ይለውጡታል። ይህ ከማስረዳት ይልቅ ያደናግራል ባይባልም፥ ከትርጉም ይልቅ ግን ማብራሪያና ሐተታ ነው ቢባል ይሻላል። ክላሬንስ ጆርደን የተባለው አሜሪካዊ 'ከትንፓች ሸርዥን' ብሎ የተረጎመው አዲስ ኪዳን በዚህ የአተረጓጎም ስልት ርቆ የሄደና በጣም የሚጠቀስ ነው። ለምሳሌ የሮሜን መልእክት ለሮሜ ሰዎች ሳይሆን በዋሺንግተን ዲሲ ላላችሁ ምዕመናን እያሰኘ ነበር የተረጎመው። አሳቡ ሮሜ የዚያ ዘመን ዋና ከተማ እንደነበረች ሁሉ ዲሲም የዚህ ዘመን የእርሱ አገር ዋና ከተማ በመሆኗ ነው። ሌሎቹንም የቆሮንቶስን፥ የኤፌሶንን ወዘተ፥ መልእክቶች በሌሎች አሜሪካዊ ከተሞች እየመነዘረ ነው የተረጎመው። ይህ ርቆ መሄድና ለዋናው ቋንቋ ደንታ ማጣት ነው። የ1972ቱ በቀላል አማርኛ የተተረጎመው ትርጉም በነጻ ትርጉምና በእኩያ ልዋጭ መካከል የሚወድቅ ይመስላል።

## ዳራና ዐውደ ምንባብ

ስለ ትርጉም በአጭሩ ይህን ካየን ወደ ዳራ እንምጣ። ዳራ ስንል ለጽሑፉ የጀርባና የአካባቢ ታሪክ ሊሆን የሚችለው ሰፊ መስክ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቢሆንም በዓላማና ለአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ለኖረ ማኅበረ ሰብ ወይም ሰው ነው የተጻፈው። ያ ማኅበረ ሰብ ወይም ሰው የነበረበትን ሁኔታ ማወቅ ስለ ተጻፈላቸው ነገር ይበልጥ ለመረዳት ይጠቅማል። ጊዜው ምን ይመስል እንደነበር፥ ያሉበት የፖለቲካ ሁኔታ፥ የአስተዳደር ሥርዓት፥ የምጣኔ ሀብት ደረጃ፥ የውጭ ግንኙነት፥ ባህላቸው ሌሎችም ነገሮች መታወቃቸው

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ይበልጥ እንድንረዳው ሊረዳ ይችላል። እነዚህን ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ከራሱ ከሚነበበው ክፍል ልናገኝ እንችላለን። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስን መልእክት ለምን እንደጻፈ በውስጡ ከጠቀሳቸው የቆሮንቶስ ምዕመናን ከጠየቁት ጥያቄዎች መረዳት እንችላለን። ስለ ቆሮንቶስ አጠቃላይ የዘመኑ ሁኔታ ይበልጥ ለመረዳት ግን የጊዜውን ታሪካዊ ጥናቶች ማጤን ሊያስፈልግ ይችላል።

ስነ ጽሑፋዊው ዐውድ ሌላው ነጥብ ነው። ይህን ይበልጥ የምናገኘው የተጻፈበትን የጀርባ ታሪክ ሳይሆን ራሱ ጽሑፉ ያለበትን አቀማመጥ በማጥናት ነው። የአንድ መጽሐፍ ሰፊ ዐውድ መጽሐፉ በሙሉው ነው። ከዚህ የሚሰፋ ዐውድም አለ፤ ያም ጠቅላላው የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ነው። የሰውን ፍጥረት፥ ውድቀት፥ ቤዛነትና ደኅንነት የሚናገር አንድ መጽሐፍ ነው። ይህን ሳንዘነጋ ነው አንድን መጽሐፍ በሙሉ ማየት ያለብን። ለአንድ መጽሐፍ ዋና አድፍገን ለጊዜው ማየት ያለብን ጠቅላላውን ወይም ሙሉውን መጽሐፍ ነው። አንድ ቃል ትርጉም የሚሰጠው ከፊቱና ከኋላው ካሉት ቃላት ወይም ሐረጎች ጋር አብሮ በመሄድ ነው። ይህ ጠባቡ ዳራ ነው። ስለዚህ አንድ አንቀጽ ወይም ጥቅስ ሲፈታ፥ ሲገለጥ፥ ወይም ሲተነተን ዙሪያው ሳይዘነጋ መሆን አለበት። ዙሪያው ብቻ ሳይሆን ጠቅላላው ያ መጽሐፍ ሳይዘነጋ መሆን አለበት። የጸሐፊው አሳብም ምን መሆኑን ማግኘት የሚቻለው ከጠቅላላው መጽሐፍ ጥናት ነው። የጽሑፉን ወይም የመጽሐፉን አከፋፈልም ጠንቅቆ ማጥናት አንድን መጽሐፍ በሥርዓት መበለትና መረዳት እንዲቻል ይረዳል።

ቀጥሎ ባሉት ገጾች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ዓይነት መጻሕፍት እንዴት ማየትና መፍታት እንዳለብን በመጠኑ እንመለከታለን።

## ብሉይ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን፥ ወይም አንዳንዶች እንደሚጠሩት የአይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ፥ በጠቅላላ 39 መጻሕፍት የሚገኙበት የቅዱሳት መጻሕፍት ስብስብ ነው። የኪዳን መጽሐፍ የሚያሰኘው በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገው የአምላክና የሕዝቡ ቃል ኪዳን ነው። ይህን በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ እናየዋለን። ኪዳኑን ብሉይ ወይም አሮጌ ያሰኘው ደግሞ ከዚህ ኪዳን በኋላ ሌላ አዲስ ቃል ኪዳን መፈጸሙ ነው። ይህ አሮጌው ቃል ኪዳን ገና በጉልበትና በሥራ በነበረበት ጊዜም እግዚአብሔር አሮጌው ኪዳን ራሱ በአዲስ እንደሚተካ ተናግሮ ነበር፤ ኤር. 31፤31-34። አሮጌው ኪዳን በአዲሱ እስኪተካ ድረስ





ግን ኪዳኑ በአይሁድና ወደ ይሁዲነት በገቡ ሁሉ ላይ ጽኑ ነበር። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የኪዳኑ ሕግ ብቻ ሳይሆን ታሪኮች፥ ትንቢቶች፥ የጥበብና የቅኔያት መጻሕፍትም ይገኙባቸዋል። እኒህን በየተራ ተከተላቸው ከአፈታት ትምህርት አንጻር እናያቸዋለን።

## የኦሪት መጻሕፍት

ከብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው የመጻሕፍት ስብስብ ሕገ ኦሪት ነው። በኦሪት ውስጥ አምስት መጻሕፍት ቢገኙም ሕግጋቱ የተከማቹት በአራቱ፥ ማለትም፥ ከዘጸአት እስከ ዘዳግም፥ በተለይም ከዘጸ. 20 እስከ ዘዳ. 33 ባለው ክፍል ነው። ኦሪት ዘፍጥረትና የዘጸአት የመጀመሪያ ምዕራፎች ምንም እንኳ አቀማመጡ በአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት ውስጥ ቢሆንም የሚመደቡት ከታሪክ ጽሑፎች ጋር ነውና ከታሪክ መጻሕፍት ጋር አብረው ይታያሉ። በዚህ ክፍል የኦሪት መጻሕፍት ሲባል እንግዲህ ሕገ ኦሪትን ወይም የሕግጋቱን ክፍል መሆኑ ነው። ኦሪት ቶውራህ תּוֹרָה ወይም ቶራህ תֹּרָה ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ይመስላል። ቶራህ ሕግ ወይም ትእዛዝ ማለት ነው። በተለይም አሠርቱ ትእዛዛትን ይመለከታል።

ከዘፍጥረት ቀጥሎ ባሉት አራት መጻሕፍት፥ በተለይም ከዘጸ. 20 እስከ ዘዳ. 33 ባሉት ምዕራፎች 613 ሕግጋትና ደንቦች ተጽፈው ይገኛሉ። የኦሪትን ሕግጋት በተመለከተ እኛ ክርስቲያኖች መረዳትና ማድረግ ያለብን ምንድርነው? ለመሆኑ እነዚህን ሕግጋት መጠበቅ አለብን ወይስ የለብንም? ከኖረብን የትኞቹን ነው መጠበቅ ያለብን? ከጠበቅናቸው ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመሆናችን ትርጉሙ ምንድርነው? ካልኖረብን ደግሞ ለምን? የሚሉ በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንችላለን። ዋናው ነጥብ ሕገ ኦሪት በክርስትና ሕይወት እንደምን ይገናዘባል ወይም እንደምን ተግባራዊ ይሆናል? የሚለው ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ከሕገ ኦሪት ትእዛዛትና ደንቦች ጋር ሲታገሉ ይታያልና የኦሪት መጻሕፍትን በተለይም የሕገ ኦሪትን አፈታት ማወቁ ጠቃሚ ነው።

ሕገ ኦሪት በመጀመሪያ ደረጃ ቃል ኪዳን ነው። ብሉይ ኪዳን ወይም አሮጌው ኪዳን የምንለው ቃል ኪዳን ዋና እንብርት ይህ የሕግ ክፍል ነው። ምንም እንኳ በብሉይ ኪዳን ውስጥ 39 መጻሕፍት ቢኖሩም ኪዳኑን ኪዳን ያሰኘው ሕገ ኦሪት ነው። ሕገ ኦሪት እንግዲህ ቃል ኪዳን ነው። በአዲሱ ኪዳን ምክንያት አሮጌው አሮጌ ቢደረግም ግን ቃል ኪዳን ነው። ጥንት ኪዳን በሁለት ሰዎች ወይም ወገኖች መካከል የሚደረግ የቃል ወይም የተስፋ መለዋወጥ ወይም መሐላ የመግባት ሥርዓት ነው። ቃል

ኪዳኑን የሚገቡት ሁለቱ ወገኖች፥ ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፥ እኩያዎች አይደሉም። አንዱ ኃያል፥ ሌላው ደካማ ናቸው። የኪዳኑ ዓላማ ጠንካራው ወገን ደካማውን ከጥቃት ሊጠብቅ፥ ደካማው ወገን ደግሞ ለኃያሉ ታማኝነትንና ታዛዥነትን ሊያበረክት ነው የሚስማሙት። ነገሩ ለእኛ የቅኝ ገዥና የተገዥን ሥርዓት ይምሰለን እንጂ በዘመኑ በተለይ ደካማው ከአጥቂዎች የሚጠበቅበት ጥሩና ጠቃሚ የኪዳን ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ከኃያሉ ወገን ለደካማው ወገን ተጽፈው የሚሰጡ በርካታ ደንቦች ይኖራሉ። ሕገ ኦሪትንም ስንመለከት እነዚህን ነገሮች በመደዳ መመልከት አይሳነንም። ሁለቱ የኪዳን ወገኖች እስራኤልና እግዚአብሔር ናቸው። ቃል ኪዳን የተገባቡትም እስራኤል እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው ከግብጽ ከወጡና ወደ ከነዓን ጉዞ ከተያያዙ በኋላ በሲና ተራራ ነው። ስለዚህ ሕገ ኦሪት እስራኤልን ወይም አይሁድን ብቻ የተመለከተ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ወደ ይሁዲነት የሚገቡትን ሰዎችም ይመለከታል። ራሳቸውን ለዚህ ኪዳን ለማስገዛት ወደው ተገይረዋል ወይም ወደዚህ እምነት ለመግባት ወስነዋልና። እንግዲህ ሕጉ እንደ ሕግነቱ እስራኤልን ወይም አይሁድን ብቻ የተመለከተ ነውና እስራኤላዊ ወይም አይሁዳዊ ያልሆንን እኛን ከቶ የሚመለከት አይደለም። በትውልድ አይሁዳዊም እንኳ ቢሆን አንድ ሰው ወደ አዲሱ ኪዳን ከገባ ከአሮጌው ኪዳን ስር አይሆንም። ክርስቲያኖች በዚህ ዘመን እነዚህን ሕግጋት እንጠብቅ ቢሉም እንኳ በሙሉ መጠበቅ አይችሉም። ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ አይሁድም ራሳቸው ሁሉን ፈጽመው መጠበቅ ከቶ አይችሉም። እንዳይቻል የሚያደርገው ዋና ውጪያዊ ምክንያት ቤተ መቅደስ ያለመኖሩ ነው። ከሕግጋቱ በርካቶቹ ከቤተ መቅደስ ወይም በዚያን ጊዜ የመገናኛ ድንኳን እና ከመቅደስ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ደንቦች ናቸው። ስለዚ እንፈጽም ቢባል እንኳ አይቻልም።

ሕገ ኦሪት እንግዲህ አሮጌው ቃል ኪዳን ነው። ብሉይ ኪዳን ነው። አዲስ ኪዳን ከኖረ አሮጌው ኪዳን አይሠራም ማለት ነው። አዲስ አዋጅ፥ ለምሳሌ፥ አዲስ የመሬት አዋጅ ሲታወጅ አሮጌው የመሬት አዋጅ አይሠራም። ኪዳኑ አልተደመሰሰም፤ ነገር ግን በአዲስ ተለወጠ፤ በአዲስ ተተካ። ሕግ ከእግዚአብሔር የመነጨ ነውና መንፈሳዊ ነው። ሆኖም ታማኝነትና ታዛዥነት ሳይቀሩ መንገዱ ግን ተለወጠ። የሮሜ የገላትያና የዕብራውያን መልእክቶች መጻሕፍት ዋና ትምህርት ይህ ነው። የቀድሞው የአጠባበቅ መንገድ የሙሴን ሕግ ወይም ሙሴ በሲና የተቀበለውን ሕግ መጠበቅ ነበር፤ አዲሱ ግን የክርስቶስን ሕግ መፈጸም ሆነ፤ ገላ. 6፥2። ስለዚህ የአዲሱ ኪዳን ሰዎች በአሮጌው ኪዳን ሕግ ሥር አይደሉም።

ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ደንቦችና የደንቦች ገጽታዎች በአዲስ ኪዳን የሚጠበቁ ከቶ የሉም ማለት ነው? የሕገ ኦሪት ትእዛዛት



ሁሉ የአዲስ ኪዳን አማኞች እንዲጠብቁአቸው የተሰጡ አይደሉም። ሆኖም የሚጠበቁ የተወሰኑ አሉ። ይህ አሳብ ቀደም ካለው ነጥብ ጋር የሚጋጭ ይመስላል፤ ግን አይደለም። የአሮጌው ኪዳን አንዳንድ ትምህርቶች በአዲሱም ኪዳን ውስጥ ተደግመዋል። ለእስራኤል የተሰጡት ሕግጋት በተለያዩ ፈርጆች ሊፈረጁ ይችላሉ። በተለይ እሦስት ዋና ዋና ቦታ ይመደባሉ። ሲመደቡ የወንጀለኛ መቅጫ ደንቦች፥ ሃይማኖታዊ ወይም የአምልኮ ሥርዓቶች እና ግብረ ገባዊ ሕግጋት ሊባሉ ይቻላል። የወንጀለኛ ወይም የጥፋተኛ መቅጫ ሕግጋት የበደለኛን ጥፋት ለመቅጣት የተደነገጉትን ይመለከታል። ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚመለከተው ደግሞ ከአይሁድ አምልኮ፥ ከመገናኛው ድንኳንና ከቤተ መቅደሱ፥ ከመስዋዕትና ከመንጻት ይህንንም ከመሳሰሉት ጋር የተያያዙ ደንቦች ናቸው። እነዚህ ሁሉቱ ፈርጆች በጣም የጠበቡና ያንን ሕዝብ ብቻና ካህናትና አገልጋዮችን ብቻ የተመለከቱ ናቸው። ሦስተኛውና ግብረ ገባዊ ሕግጋት የሚባሉት ግን ሰፊ አድማስ ያላቸውና በሁሉ ዘንድና ሁልጊዜ ሊጠበቁ የተገባቸው ዓይነት ናቸው። እነዚህ ግብረ ገባዊ ሕግጋት በአዲሱም ኪዳን ውስጥ እንዲጠበቁ ተደግመዋል፤ እንዲያውም ጠንክረው ተደግመዋል። እነዚህ የሚጠበቁት እዚያ የተጻፉ ቢሆኑም እዚህ ስለተደገሙ ነው። አሠርቱ ትእዛዛት፥ በተለይም ከሰንበት በቀር ዘጠኙ፥ እንዲሁም ሕግና ነቢያት የታሰሩባቸው የተባሉት ሁለቱ እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ በግልጽ በአዲስ ኪዳንም የተጠቀሱትና በአዲሱ ኪዳን ሕዝብም በትጋት እንዲፈጸሙ የሚጠበቁት ናቸው።

እንዲህ ከሆነ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን የሚባለው ብቻ መሆን አለበት ማለት ነው? አይደለም። ሕገ ኦሪት ወይም አሮጌው ኪዳን ለአዲሱ ኪዳን ሰዎች የተሰጠ ትእዛዝ ባይሆንም እንኳ በአፊዎት የተጻፈ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የእግዚአብሔር ቃል ነው። ለትምህርትና ለተግሳጽ፥ ልብን ለማቅናትና በጽድቅም ላለው ምክር የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሕጉ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት ይኖሩ ዘንድ ይፈልግ እንደነበር ለምሳሌነትና ለትምህርት ተጽፎልናል። ግልጽ የሆኑ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚያሳዩንን ባህርያቱን በሕጉ ውስጥ እናያለን። እስራኤል እንዳያደርጉአቸው ከተነገሩአቸው በርካታ ነገሮች አንዳንዱ የማይገቡን ናቸው፤ ሆኖም ጥልቅ ለሆነ ጥንቃቄና በዙሪያቸው ከነበሩ አሕዛብ የተለዩ ለመሆናቸው መታወቂያ ተደርገውም የተሰጡ ናቸው። እስራኤል እነዚህን ነገሮች ቢያደርጉ እንደሚባረኩም ተስፋ ተሰጥቶአቸዋል። ባይጠብቁ ደግሞ መርገም እንደሚጣበቅባቸውም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። የእስራኤልን ታሪክ ስንመረምር ባለመጠበቃቸው ምክንያት የተባሉት መርገሞች ሁሉ እንደደረሱባቸው እናያለን። ይህ ሁሉ ስለመታዘዝ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን ነው።

ብሉይን ወይም ሕገ ኦሪትን ማንም ጠብቆ መዳን አይችልም። ከአዲስ ኪዳን አንጻር ስናየው ሕጉ የተሰጠው ሰው ጠብቆት እንዲድን ሳይሆን ደካማነቱን እንዲያውቅና ወደሚያድነው አምላክ እንዲቀርብ ነው። ሕግን ፈጽሞ የጠበቀ በደሙ አዲሱን ኪዳን የመሠረተው ክርስቶስ ብቻ ነው። ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ከኦሪት መጻሕፍት፥ በተለይም ከሕገ ኦሪት ሲያስተምሩ እነዚህን ነገሮች መረዳትና ማስረዳት አለባቸው።

# የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት

በሰፊውና በጥቅሉ ከወሰድነው መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉው አንድ የታሪክ መጽሐፍ ነው ለማለት ይቻላል። በአጠቃላይ ፍጥረትን፥ ውድቀትንና ቤዛነትን የሚናገር አንድ ትልቅና ድንቅ ታሪክ ነው። ወደ ውስጥ ስንዘልቅ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የታሪክ መጻሕፍት ወይም የትረካ ጽሑፎች የምንላቸው የተለየ የአጻጻፍ ስልት የያዙ መጻሕፍት ይገኛሉ። እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ሰፊ ቦታ ይዘዋል። ከብሉይ ኪዳን አሥራ አምስት ያህሉ የትረካ መጻሕፍት ናቸው። ዘፍጥረት፥ ከኢያሱ እስከ አስቴር ድረስ ያሉት መጻሕፍት በሙሉ እንዲሁም ዳንኤል ዮናስና ሐጌ የታሪክ መጻሕፍት ናቸው። ሌሎችም በርካታ መጻሕፍት ለምሳሌ፥ ዘጸአት፥ ዘኁልቁ፥ ኢዮብ፥ ኢሳይያስ የተወሰኑ የትረካ ክፍሎች አሉአቸው።

እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተጻፉ ሆነውም እንደማናቸውም የታሪክ ስነ ጽሑፎች የትረካ ስልትን የተከተሉ ናቸው። በውስጣቸውም መቼት (setting) ፥ ጥሩና መጥፎ ገጸ ባሕርያት (characters) እንዲሁም ሴራ ጽሑፍ (plot) የያዙ ናቸው። የታሪክ መጻሕፍት ዋና ዓላማቸው የተፈጸሙ ድርጊቶችን መግለጥ ሆኖ በዚያ ውስጥ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሥራ ማሳየት ነው። በእነዚህ የትረካ መጻሕፍት እግዚአብሔር በፍጥረት ሥራው፥ በሕዝቡ ውስጥ በመለኮታዊ ኃይለ ገባዊ ሥራው፥ እንዲሁም በማዳን ዕቅዱና ተግባሩ በገሃድ ይታያል። የመጻሕፍቱ ግብ ከተደረጉት ወይም ከተከናወኑት የተፈጸሙ ሥራዎች ጎን ይህን መግለጥም ነው። ይህ እግዚአብሔርን እንድናውቅና እንድናደንቅ፥ እንድናመልከውም ያደርገናል። ከነጠላ ታሪኮቹም ለሕይወታችን የምንቀስማቸው በርካታ ትምህርቶች አሉ።

የትረካ መጻሕፍት የተለያዩ ደረጃዎችን የያዙ ናቸው። በመጀመሪያ ነጠላ ታሪኮችን እናገኛለን። ለምሳሌ፥ የዮሴፍ መሸጥ፥ የሳምሶን መታወር፥ የአስቴር መመረጥ፥ የዮናስ አለመታዘዝ፥ ወዘተ። እነዚህ ለየብቻ ልንመለከታቸው የሚቻሉ ነጠላ ታሪኮች ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የታሪክ መጻሕፍት በሙሉ የአንድ





ሕዝብ ታሪክ ስብስብ ናቸው። ያም ሕዝብ እስራኤል ነው። ስለዚህ የታሪክ መጻሕፍት የእስራኤል ታሪክ መጻሕፍት ናቸው ማለት ነው። ከአብርሃም ጥሪ ጀምሮ እስከ አዲስ ኪዳን ጅማሬ ድረስ የሚገኝ የአንድ ሕዝብ፥ የእስራኤል ታሪክ ነው። ሦስተኛውና ሰፊው ደረጃ የታሪክ መጻሕፍትም ሆኑ አዲስ ኪዳንን ጨምሮ ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ በመላው አንድ ታሪክ ነው። ያም የእግዚአብሔር ሥራ ታሪክ ነው። የፍጥረት፥ የውድቀትና የቤዛነት ታሪክ፤ ዋናው ገጸ ባሕርይ እግዚአብሔር የሆነበት ሰፊና ትልቅ ታሪክ ነው። ይህ 'ትልቁ ስዕል' ነው። እንግዲህ እያንዳንዱ ነጠላ ታሪክ የእስራኤል ታሪክ አካል ነው። የእስራኤል ታሪክም የእግዚአብሔር ሥራ አካል ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ወይም ትልቁ ስዕል እስከ አዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሥራ የደረሰና ከዚያም አልፎ የሚዘልቅ ታሪክ ነው።

የትረካ ጽሑፍ ሲጠና ጤናማና ትክክለኛው መንገድ ነጠላውን ታሪክ መውሰዱ ሲሆን ከዚያ የሰፋው ዐውድ ግን ሳይዘነጋ መሆን አለበት። እንደሌሎች መጻሕፍት ሁሉ በታሪክ ጽሑፎች ውስጥ ዐውድ ትልቅ ስፍራ አለው። አንድን ታሪክ ቀንጭበን ከሙሉው ታሪክ ውስጥ ካወጣነው ታሪኩ የማያስተምረውንና እኛ የፈለግነውን እንዲል ልናደርግ እንችላለን። አንዱ ታሪክ ከአንዱ ጋር የማይገናኝ ቢመስልም ከትልቁ ስዕል አንጻር ሲታይ በሆነ ሐረግ አንዱ ከቅርብ ወይም ከርቀት ከሌላው ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ለምሳሌ የሩት መጽሐፍ የነሩትና ኑኃሚን ታሪክ ብቻ ሳይሆን በመጽሐፉ መጨረሻ እንደምናገኘውና ከትልቁ ስዕልም እንደምንረዳው እስከ ዳዊትና እስከ አዲስ ኪዳንም የዘለቀው የክርስቶስ ትውልድ ሐረግ የተቋጠረበትም ጭምር ነው። የእግዚአብሔር የማዳኑ መንገድ የቀጠለበት መስመር ነው።

ከዐውደ ወጥነት ጋር የሚሄደው ሌላ ችግር መራጭነትና ደራችነት ነው። እንዲህ ያለው አተረጓጎም ብዙ ጊዜ በርዕሳዊ ትምህርቶችና ስብከቶች ዘንድ የሚታይ ነው። በተሳሳተ አፈታት ውስጥ ተደጋግሞ የሚታየው አንድ ችግር ይህ የማይገናኙ ክፍሎችን ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጎችን ስለያዙ ብቻ እንደ ድሪቶ ማገናኘትና መስፋት ነው። እንዲህ ያሉት አቀራረቦች ብዙውን ጊዜ ከራስ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ ተብለው የሚደረጉ ናቸው። ሁሉ ቃልም ከሕይወት ጋር የሚገናዘብ በሚመስላቸው አስተማሪዎች ዘንድ እንዲህ ያሉ ስሕተቶች ይፈጠራሉ።

በታሪክ ጽሑፎች ውስጥ የሰዎችን ሥራ ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ሥራ በስተጀርባ ሁሌም እግዚአብሔር መገኘቱን እናስተውላለን። ፊት ለፊት ወይም በስተጀርባ እግዚአብሔር የሌለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከቶ የለም። ስለዚህ ነው ትልቁ የትረካ መጻሕፍት ገጸ ባሕርይ እግዚአብሔር የሆነው። የእግዚአብሔር ስም ባልተጠቀሰበት በመጽሐፈ አስቴርም እንኳ ዋናው ባለታሪክ አስቴር ወይም መርዶክዮስ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ነው። በመጽሐፉ

ውስጥ የሆኑት ነገሮች እንዲሆኑ ያደረገ የሰው ያልሆነ ስውር እጅ መኖሩ በገሃድ ይታያልና። በሕገ ኦሪትና በሌሎችም ቦታዎች የተጻፉትን በርካታ የእግዚአብሔር ባሕርያት በተግባር በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ እናያቸዋለን።

<u>ታሪክ ታሪክ እንጂ ምሳሌ ስላልሆነ እንደ ምሳሌ ጽሑፎች ወይም ንግግሮች መፍታት የለብንም።</u> በአንዳንድ የታሪክ ጽሑፎች ውስጥ የተደረጉትን ነገሮች በጥሬው ብቻ እናገኛለን እንጂ እንዴትና ለምን እንደተደረጉ ዝርዝር አናገኝም። ስናነብባቸውም ሙሉና ግልጽ አይመስሉን ይሆናል። እነዚህ ግልጽ ያልሆኑ ወይም ሙሉ ያልመሰሉን ታሪኮችም በራሳቸው ታሪኮች ናቸው እንጂ ትርጉም የሚሹ ምስጢሮች አይደሉም። ታሪኮች ታሪክ እንጂ ምሳሌ አይደሉምና እንደ ምሳሌ መፈታት ወይም መተርጎም የለባቸውም። እንዲህ ከተደረገ ወዳልተጠበቀና ጤናማ ያልሆነና የተሳሳተ ድምዳሜ ያደርሰናል። ምሳሌ ወይም ተምሳሌትን በተመለከተ በእርግጥ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሲጠቀሱ እንደ ምሳሌ ተደርገውና ሙሉ ትርጉም ተሰጥቶአቸው ተብራርተዋል። ለምሳሌ እስራኤል ከዓለት ውኃ መጠጣታቸው በብሉይ ኪዳን ሲጻፍ ዓለቱ ዓለት ብቻ እንጂ ሌላ ምንም መሆኑ አልተነገረም። በብሉይ ኪዳን እንደተጻፈው ያ ዓለት ዓለት ብቻ ነው። በአዲስ ኪዳን ግን ጳውሎስ ይህን ታሪክ ሲጠቅስ ይህ ዓለት ይከተላቸው የነበረው ዓለት ወይም ክርስቶስ መሆኑን ጠቅሶ ያብራራል። ጳውሎስ ሲጽፍ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጠለት ዓለቱ ውኃን ያጠጣቸው የክርስቶስ ተምሳሌት መሆኑን በመጥቀስ ማስተማሩ ነው። እዚያ ዓለት የተባለውን እዚህ ክርስቶስ ይለዋል። ጳውሎስ ይህን ማለቱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እየጻፈ ነውና እንዲህ ማድረግ ይችላል። እኛ ግን እንዲህ ያለ ትርጉም መስጠት አንችልም፤ ምክንያቱም፥ እኛ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተን የተጻፈውን ቃል እየሰበክን ወይም እያስተማርን ወይም እየተማርን ነን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን እየጻፍን አይደለንም። የኛው አብርሆት እንጂ አፊዎት አይደለም። አፊዎት ለመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ወይም የተደረገ ምሪት፥ መነዳት ወይም በሚጽፉት ነገር ላይ የመለኮታዊው እስትንፋስ ማረፍ ሲሆን አብርሆት ደግሞ ያው አንዱ መንፈስ ጸሐፊው የጻፈውን አንባቢው መረዳት እንዲችል የሚሰጠው የአስተውሎት ልቡና ነው። እንዲህ በታሪክ መጻሕፍት የተጻፈውን ዓለቱን፥ በጉን፥ ዛፉን ክርስቶስ፤ ፍየሉን፥ እሳቱን፥ ነፋሱን ሰይጣን እያልን ልንተረጉም አንጣር። በዚያ የታሪክ ክፍል ውስጥ የተጻፈው ቋንቋ ምሳሌያዊ ከሆነ ተጠንቅቆ ማየትና መፍታት ተገቢ ሲሆን ምሳሌያዊ ያልሆነውን እንደ ምሳሌ ወስደን ሌላ ነገር አድርገን ካስተማርን ግን ስተን እናስታለንና ልንጠነቀቅ ይገባናል።

ከላይ እንዳየነው አንዳንዶቹ ታሪኮች በእርግጥም ያላለቁ፥ የተጎመዱ፥ እመሃል የቀሩ ናቸው። የአንዳንዶቹን ባለታሪኮች መጨረሻ ብናውቅ ደስ ይለን ነበር። ግን አልተጻፈም።





ያልተጻፈውን ዝምታም እንዳለ መቀበል አለብን። እኛ ለማወቅ የፈለግነው የቀረ ቢመስለንም እንኳ እግዚአብሔር እንድናውቀው የፈለገውን እንዲጻፍ አድርጎአል። ልናውቅ ከሚያስፈልገን አንጻር ሲታይ ታሪኩ ሙሉ ነው። የምንፈልገው ባይጻፍም የሚያስፈልገን ተጽፎአል።

የታሪክ ጽሑፎች ጎዶሉ መምሰል ብቻ ሳይሆን በብዙ ቦታዎች በግልጽ ቢናገሩም በአንዳንድ ቦታዎች ጠቁመው ወይም አመልክተው ብቻ ያልፋሉ። በእነዚህ የጎንዮሽ ተጠቁመው በሚያልፉ ታሪኮች ትምህርት ላይ ጠንቃቃ ልንሆን ያስፈልጋል። ነገሮቹ ተጠቆሙ ወይም ተመለከቱ ሲባል በጥቂት ቃላት ብቻ ተነገረዋል፤ በግልጽና በብዙ ቃላት አልተጻፉም ማለት ነው። እነዚህን በጥቂት ቃላት የተጻፉና የታለፉ ነገሮች ሰባኪዎችና አስተማሪዎች መለጠጥና ያላሉትን እንዲሉ ማድረግ የለባቸውም።

ከዚሁ ከመጠቆም ጋር የሚያያዘው ሌላ ነጥብ ባህላዊና የወግ ልማዶችን በስሱ አመልክተው የሚያልፉ ክፍሎች መኖራቸው ነው። ለምሳሌ ቦዔዝ ጫማ አውጥቶ መስጠቱ፥ ወይም አብርሃም ቄብ ፍየሎች ማቆሙ እንዲሁም ይህን የመሳሰሉት ልማዳዊና ባህላዊ ድርጊቶች በቃሉ ውስጥ ሳይብራሩና ሳይተነተኑ ተጽፈው ብቻ እንዳለፉ እናስተውላለን። ጽሑፎቹ የታሪክ ጽሑፎች ናቸውና ታሪኩን ነው እየተረኩልን ያሉት እንጂ የባህል ምርምር ወይም የወጎች ጥናት ጽሑፎች ባለመሆናቸው ስለነዚህ ነገሮች ምንም ማብራሪያ አልተውልንም። ታሪካዊ ዳራውንና የዘመኑን ልማድና ባህል ካልተረዳን እንዲህ ያሉትን ክፍሎች በተሳሳተ መንገድ ልንፈታ እንችላለንና እነዚህን ባህላዊ ጉዳዮች መረዳቱ ተገቢ ይሆናል። በተሳሳተ ሁኔታ መፍታት ብቻ ሳይሆን ባልተገባ ሁኔታ ከሕይወታችን ልናገናዝብና ልንለማመድም እንጋበዝ ይሆናል። ይህ ዝንጀሮ ያየውን ሊያደርግ ሲሞክር በላዩ አደጋ ሊያመጣ እንደሚችለው 'የዝንጀሮ ኩረጃ' አጉል ሁኔታ ውስጥ ሊጥለን ይችላል። የእስራኤል ታሪክ ሁሉ የኛ ታሪክ ፈር አይደለም። እነርሱ ያደረጉትንና የሆኑትን ሁሉ እኛም እናደርጋለን፥ እንሆናለን ማለትም ፈጽሞ አይደለም። ምንም እንኳ የሚቀራረቡባቸው መልኮች ሊኖሩ ቢችሉም የያኔው የእነርሱ ባህልና የዛሬው የእኛ ባህል አንድ አይደሉም። ደግሞም እንደ ጥንቱ ሁሉ ዛሬም መጥፎና ጥሩ ባህል አለ። አጥፍተው የተቀጡና ተሳስተው የተማሩ ሰዎችም አሉ። የኛ ግብ ከእነርሱ ሕይወት መማርና ጠቃሚውን መቅሰም እንጂ የሆኑትን ሁሉ መሆን አይደለም። ልንመስላቸው ከተገባን የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከትን በፍለጋቸው ልንሄድ እንችላለን። ሆኖም ታሪካቸው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መገኘቱ እኛን እንደ እነርሱ የማድረግና የመሆን ግዴታ ውስጥ አያስገባንም። ወደ ቃሉ ግዴታ ውስጥ የሚያስገቡን በግልጽና በዝርዝር የተጻፉ ትምህርቶችና ትእዛዞች ናቸው። ታሪኮቹ እንደ ዋና ዓላማቸው የእግዚአብሔርን በሰዎች ታሪክ ውስጥ መግባትና

መሥራት ማሳየትና ከዚያም እንድንማር ማድረግ ነው እንጂ የአዲስ ኪዳን አማኞችን እነዚያን ታሪኮች እንድንደግም የሞራል ግዴታ ውስጥ የሚያስገቡን አይደሉም። ለምሳሌ ኮሪያዊው መጋቢ ፖል ዮንጊ ቾ በዘፍ. 30፥25-43 የሚገኘውን የያዕቆብንና የላባን በጎችንና ፍየሎች ታሪክ በመውሰድ 'የማየት ሕግ' የሚባለው ትምህርቱ ዋና ምሳሌ በማድረግ አቅርቦታል። በዚህ ዘመን የምንገኝ አማኞችም እንደ ያዕቆብ የማየትን ሕግ በመለማመድ ያልኖሩ ነገሮችን ወደ መኖር ማምጣት እንደምንችል አስተማረ። በምዕ. 31፥1-12 ያለውን ስንመለከትና በሕልሙ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገረውን ክፍል ስናነብ ግን የበጎቹና የፍየሎቹ እንደዚያ ያሉ ግልገሎችን መውለድ እግዚአብሔር በደሉን አይቶ የካሰው መሆኑ በግልጽ ይታያል። እንግዲህ ከተፈጸሙ ታሪኮች የምንማረው ነገር ቢኖርም በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች እንዳሉ እንድናደርጋቸው ካልተጻፉልን በቀር ልንደግማቸው አይገባንም፤ አይጠበቅብንምም።

<u>የታሪክ ጽሑፎች ታሪኮች እንጂ ትምህርቶች ወይም የአስተምህሮት ዋና ፍሬ አይደሉም። ምንም እንኳ ለትምህርታችን ቢጻፉና ከተጻፈው ነገር ትምህርትን ወይም ልምድን ልንቀስም ብንችልም የአስተምህሮት ዋና መገኛ አይደሉም።</u> ታሪኩ በሌላ ቦታ እንደ አስተምህሮት ለምናገኘው ነገር አስረጅ ታሪክ ሊሆን ይችላል። ማለትም፥ ታሪኮቹና በታሪኮቹ ውስጥ ያሉት ጭብጦች ለቅምር ወይም ስታዊ ስነ መለኮት (systematic theology) ማዳበሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ስለ ሰው ባሕርይ ሲጠና የዮናስ ታሪክ ስላለመታዘዝ መጥፎነት፤ የዮሴፍ ወንድሞቹን በፍቅር መቀበል ስላለመበቀል ወይም በፍቅር ስለመቀበል መልካምነት፥ ዳንኤል ስለ ጽንዓት ምሳሌ በመሆን ሊረዱ ይችላሉ እንጂ ታሪኮቹ በዋናነት በራሳቸው አስተምህሮት አይደሉም። እንደ ታሪካዊ አስረጅነታቸው ብንወስድም እንኳ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጻፈ ብቻ ጥሩና ትክክል ነው ብለን መውሰድም የለብንም። ስለተጻፉ ብቻ ጥሩና ትክክል ነው ብለን የተደረጉትን ነገሮችም ሁሉ በጭፍን ምሳሌነት አለውና ብለን የተደረጉትን ነገሮችም ሁሉ በጭፍን መከተልም የለብንም። እንደ ጌዴዎን ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅ የበግ ጠጉር ውጪ ማሳደር፥ እንደ ሶምሶን የአህያ መንጋጋ አንስተን የሚጠሉንን ክምር በክምር ላይ ማድረግ ወይም ዳዊት የጠሉትን ሰዎች ራሱ ሳይቀጣ በሰሎሞን እንዳስቀጣቸው 'ጥበብ የተሞላበት' ማድረስ አለብን ማለትም አይደለም። የአንዳንዶቹ ሰዎች ባህርይ እና ሥራ ከበጎ እጅግ የራቀ ነው። ከታሪካቸው የምንማረው አለ፤ ምሳሌነታቸውን እንዳንከተል ግን የቃሉ ምክር ያስረዳናል። እንግዲህ ታሪኮች ወይም የታሪክ መጻሕፍት አስተምህሮታዊ ወይም የስነ መለኮት ጥያቄዎቻችንን ሁሉ አይመልሱልንም። አንዳንዴ እንዲያውም መልስ ከሚለግሱን ይልቅ በተቃራኒው ለምንና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች ነው የሚሞሉን። ለአስተምህሮታዊና ስነ መለኮት ጥያቄዎቻችን አጥጋቢ





መልሶችን ማግኘት የምንችለው በትምህርታዊ ወይም አስተምህሮታዊ ጽሑፎች ውስጥ ነው።

# የሀዝሙራትና የጥበብ መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ሲባል የተጻፈው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወይም ነጂነት ነው እንጂ የተጻፈው ሁሉ እግዚአብሔር ለሰዎች ቃል በቃል የተናገረው ቃል ነው ማለት አይደለም። አንዳንዱ ክፍል ሰዎች ለእግዚአብሔር ወይም ስለ እግዚአብሔር የተናገሩትም ነው። አንዳንዶች የምስጋናና የውዳሴ፥ የጸሎትና የልመና ቃላት ናቸው። አንዳንዶቹም ሊዘመሩ የተደረሱ ድርሰቶች ናቸው። መዝሙረ ዳዊት እንዲህ ያሉ መዝሙሮች ስብስብ ነው። መዝሙሮቹ በሰዎች ቢደረሱም የመጀመሪያዎቹን ጸሐፊዎች ሥራ የተቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንደገና እናስተውል። በዚህ ክፍል፥ ማለትም፥ በመዝሙራትና የጥበብ መጻሕፍት የሚገኙት መጻሕፍት መዝሙረ ዳዊት፥ መኃልየ መኃልይ፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ፥ ኢዮብ፥ ምሳሌና መክብብ ናቸው። የእነዚህ መጻሕፍት አጻጻፍ ከጥቂት ቦታዎች በቀር በቅኔ ወይም በግጥም መልክ ነው። ግጥም ወይም ቅኔ በብዙ ኅብረተ ሰብ ዘንድ የተወደደ የአሳብ መግለጫ ነው። በአንዳንድ አገሮች ብሔራዊ ታሪኮች ጭምር በግጥም ተጽፈው ይነበባሉ፥ ይዜማሉ፥ ወይም ተሰንደው ይቀመጣሉ። ግጥም ለመያዝ የሚመች እጀታ እንዳለው መሳሪያ ያለ ስነ ጽሑፍ ነው። አንዴ ከተያዘም እንደተያዘ ሊቆይ የመቻል ውስጣዊ ተሰጥዖም አለው። በእርግጥም ቅኔና ግጥም ከስድ ጽሑፍ ይልቅ ተይዞ ይከርማል። በቀድሞዋ እስራኤል የዚህ ዓይነቱ አጻጻፍ ተገቢ ቦታ እንዳለው ታሪካቸውም መጽሐፍ ቅዱሳችንም ይመሰክራል። ይህን ያደርጉ የነበረው ለማስተማር ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን ስለተረዱ ነው። ጠቃሚ የሚሉአቸውን ነገሮች በግጥም መልክ ይነድፉአቸዋል። ውበት የግጥም ስነ ጽሑፋዊ ቁንጅና ሲሆን በቀላሉ መያዝ ደግሞ አእምሮአዊ ጥቅሙ ነው። ከዚህ አጻጻፍ የተነሣ ነው አብዛኞቻችን በቃል ከምናውቃቸው ጥቅሶች ይልቅ በቃል የምናውቃቸው አዝማቾች ወይም መዝሙሮች የሚበልጡት። ዜማ ሲጨመርበት ደግሞ የአጻጻፍ ስልቱም ታላቅ የመጨበጥ ኃይል ወይም ስፍራ ይኖረዋል። በጥንትዋ እስራኤል ጽሑፍንና መጽሐፍን በግል እንደልብ ማግኘት ቀላል አይደለምና እግዚአብሔር ቃሉ እንዲህ እንዲጻፍ ማድረጉ ጥበቡ ነው።

በመጀመሪያ የመዝሙሮችን መጻሕፍት ለማየት የመዝሙርን ምንነት እንመልከት። መዝሙሮች ጸሎት፥ ልመና፥ ምስጋናና ውዳሴ በዜማና በዝማሬ የቀረቡባቸው ጽሑፎች ናቸው። ስለዚህም፥ አንደኛ ለዜማ ነው የተጻፉት፤ ሁለተኛም በግጥም ነው የተጻፉት።

እነዚህ መዝሙሮች በመጀመሪያ ሊዘመሩ ነው የተጻፉትና ዜማ አላቸው። ከመዝሙረ ዳዊት በብዙ መዝሙሮች አናት ላይ የተጻፉት ማስታወሻዎች፥ ለምሳሌ፥ ስምንተኛ፥ ሙትላቤን፥ ምስጢር፥ አታጥፋ፥ ወዘተ፥ የሚሉ ቃላት ከዜማ ቅላጼ ወይም ቅኝት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ሊቃውንት ይጠቅሳሉ። ዜማ ለስሜት የቀረበ ነገር ነውና ስሜትም ይነበብበታል። ስለዚህም በብዙ መዝሙሮች ኃዘን፥ ደስታ፥ ጸጸት፥ ፍርሃት፥ ንዴት፥ ወዘተ፥ ይገኙባቸዋል። ሰቆቃወ ኤርምያስን ብንወስድ በሙሉ ሰቆቃ፥ ማለትም፥ የኀዘን ሙሾ ወይም እንጉርጉሮ ነው። ሁሉም ግን በዚያ ሁኔታ ተቀርጸውም ማምለኪያ ናቸው። መዝሙሮች ለአምልኮ የተሰናዱ ጽሑፎች ናቸው። እግዚአብሔር የሚመለክ አምላክ ነውና እርሱን በዜማ ወይም ያለዜማ ለማምለክ በጣም ይረዳሉ።

የአጻጻፋቸው ስልት ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው በግጥም ነው። ግጥሞች በጥንቃቄ በተለቀሙና በልክ በተከረከሙ እንዲሁም ሚዛን የጠበቁ መዋቅሮች ወይም ረድፍ የተከተለ አሰላለፍ በያዙ ቃላት የተሠሩ ናቸው። በዚህ ረገድ የየትኛውም ቋንቋ ቅኔና ግጥሞች ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ ቋንቋ ደግሞ የየራሱ የተለየ የግጥም ባህርይ አለው። የአይሁድ የግጥም ስልት ወይም አጻጻፍ በእኛው ዘንድ ከተለመደው የግጥም አጻጻፍ የተለየ ነው። የእኛ ግጥሞች በመደምደሚያ ድምጽና ቃላት መገጣጠም ወይም ቤት መምታት ላይ ያተኩራሉ። የአይሁድ ግጥሞች ደግሞ ከቃላት ይልቅ በአሳብ መገጣጠም ላይ ነው የሚያተኩሩት። ስለዚህም ነው አንዳንዴ አንዳንድ አሳቦችና ሐረጎች ሲደጋገሙ፥ ሲገመዱ፥ ላይ በላይ ሲደራረቡ፥ አንድ አሳብና የአሳቡ ተቃራኒ ተከታትለው የምናገኘው። ከዚህ ሌላም በሁሉም የግጥም ጽሑፎች ተምሳሌታዊና ስዕላዊ ቋንቋ እናገኛለን።

የአይሁድ ወይም የዕብራይስጥ ግጥሞችም ከሌሎች ጋር ከሚጋሩአቸው ስልቶች በተጨማሪ ከአሳብ መገጣጠም ሌላ የተለያዩ የግጥም አጻጻፍ ዘይቤዎችም ይጠቀማሉ። ከጥቂት ምሳሌዎች ጋር የሚከተሉት ይገኛሉ፤ ተምሳሌቶች፥ መዝ. 18፥2፤ 23፥1፤ 42፥1፤ 91፥4፤ አጋኖዎች፥ መዝ. 6፥6፤ ምስስሎች፥ ንጽጽሮችና ድግግሞሽ፥ መዝ. 9፥2፤ 11፥2፤ 13፥1-2፤ 27፥1፤ 29፥፥3-9፤ 136፤ ምሳ. 15፥25-33፤ ተመሳሳይ ድምጽ የሚፈጥሩ ቃላትን ደጋግሞ መጠቀም፥ መዝ. 10፥8-18 (ድጋ)፤ መክ. 1፥2 እና 3፥1-8፤ በተመሳሳይ ፊደላት በሚጀምሩ ቃላት ወይም በአበገደ አካሄድ በእያንዳንዱ ፊደል የተወሰኑ መስመሮችን እየጻፉ መግጠም፥ መዝ. 34፤ 119፤ ምሳ. 30፥10-31 እና ሰቆቃወ ኤርምያስ በሙሉ። በቁጥሮሽ መግጠም፥ ምሳ. 6፥16፤ 30፥7-31። እነዚህ ጥቂት ናሙና ብቻ ናቸው።





በመዝሙር ወይም በቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ተግባራዊ ትምህርቶችንም እናገኛለን፤ ለምሳሌ መዝ. 1፤ 34፥ 37፥ 73፥ 119፥ ወዘተ። ሆኖም እነዚህንም ጨምሮ መዝሙሮች በመጀመሪያ ደረጃ የተጻፉት ወይም የተገጠሙት ለዝማሬና ለአምልኮ እንጂ ለአስተምህሮት አለመሆኑን መዘንጋት የለብንም። ከመዝሙራት ታላላቅ ምክርና እዝናትን እናገኛለን፤ ልብን በእግዚአብሔር ፊት የማፍሰስን ታላቅነትም እንማራለን። በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔርን ስለማምለክም ያስተምሩናል። ቃላቱን በማሰላሰልም ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ እንዲኖረን ይረዱናል። ቀድሞም በግጥምና ለዝማሬ መጻፋቸው በልብ እንዲያዙ ለመርዳትም ጭምር ነው። ከብዙ ጥቅስ ይልቅ ብዙ አዝማቾች የምናውቀው በተመሳሳይ መንገድ ነው። ቃሉን በዜማም ሆነ ያለዜማ ማሰላሰል ተገቢ ነው። በአዲስ ኪዳንም ይህንን እንድና ደርግ ተነግሮናል ኤፌ. 1፥16 እና 5፥20። ሁሉ ሲቀሩም አምልኮና ዝማሬ የማይቀሩና ከሞት ማዶም የሚኖሩ ነገሮች ናቸው።

መዝሙሮችን ስናጠና አንዱን መዝሙር በሙሉ መመልከት አለብን። ምክንያቱም እያንዳንዱ መዝሙር በራሱ ሙሉ መዝሙር ነውና ተበጣጥቆ የሚወሰድ አይደለም። በመጽሐፈ ምሳሌ የምና ገኛቸው ምሳሌዎች ተለያይተው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው። ምሳሌዎች ልክ በክር ውስጥ እንደሚገኙ ጨሌዎች ወይም ዶቃዎችን ይመስላሉ። አብረውም ሲሆኑ ጌጥ ናቸው፤ ለብቻቸውም ራሳቸውን ይችላሉ። መዝሙሮችን በተገቢ ሁኔታ ለማጥናት ግን ሳይሰባበሩ መወሰድ አለባቸው። አንዳንድ ዘማሪዎች በመዝሙራት ውስጥ የተጻፉትን ቃላት ወይም አሳቦች እንዳለ በመውሰድ በቋንቋችን እንድንዘምራቸው አድርገዋል። ይህ የሚያስመሰግን አደራረስ ነው፤ ሆኖም የዚያ መዝሙር ትምህርት ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም፥ የኛ ደኅንነት ከተገለጠበት ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ጋር ይሄዳሉ ወይስ አይሄዱም ብሎ መጠየቅ ተቀዳሚ መሆን አለበት። አንዳንድ የአምልኮ መዝሙሮቻችን ይህን መንገድ ይዘው ርቀው ሲሄዱ ይስተዋላል። ለምሳሌ፥ አንድ ዘማሪ በአዝማቹ ላይ፥ ‘አሳዳጆቼ በማይረሳ ጉስቁልና ይጎሳቆላሉ’ ሲል ተቀባዮቹ ደግሞ ደጋግመው፥ ‘አሜን ይጎስቁሉ፥ አሜን ይጎስቁሉ’ እያሉ ተቀብለው አስተጋብውታል። በእርግጥ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ አንዳንድ የበቀል ልመና መዝሙሮችን እናገኛለን። ለምሳሌ፥ መዝ. 137፥7-9። የዚህን ምክንያትም ከታሪካቸውና ከጊዜያቸው ሁኔታ መረዳት እንችላለን። እነዚህ መዝሙሮች እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ቅጣትን እንዲያመጣባቸው የተደረጉ ልመናዎችም ናቸው። ይህ ግን በአዲስ ኪዳን ከተገለጠው ጠላቶችን ስለመውደድ፥ የሚረግሙንን ስለመመረቅ፥ ለሚጠሉን መልካም ስለማድረግ፥ ለአሳዳጆቻችን ስለመጸለይ ከሚናገረው ትምህርት ጋር ይቃረናል። ስለሚያሳድዱን የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ማለትን በአሜን ይጎስቁሉ መለወጥ አግባብ አይደለም።

የመዝሙሮች ደራሲዎች ዘማሪ ብቻ ሳይሆኑ በመዝሙራቸው አማካይነት እንደ አስተማሪም በመሆናቸው ጠንቃቃነት ይጠበቅባቸዋል። ካልበሰሉ የዜማ ቅኔዎች የሚመጡ ችግሮችን በትንሹ በሌላ ገጽ እንመለከታለን። የመጽሐፍ ቅዱስ የመዝሙሮችና የቅኔያት መጽሐፍ ሲጠና እንደገና ትልቁን ስዕል ማየት ተገቢ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው ሰቆቃወ ኤርምያስና መኃልየ መኃልይም መዝሙሮች ናቸው። ሰቆቃወ ኤርምያስ በኛ መጽሐፍ ቅዱስ አቀማመጥ ከነቢያት ጋር ተመደበ እንጂ በአይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽሑፎች ወይም 'ክታቦች' በሚባሉት ምድብ ነው የሚገኘው። መጽሐፉ እንደ ስያሜው ሰቆቃ፥ ልቅሶ ወይም የኀዘን ሙሾ ነው። ስለፈረሰች ከተማና ስለተጠቃ ሕዝብ በማልቀስ ስለጥፋት ንስሃና በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለመገዛት እንዲሁም የመኀብኘትን ልመና ያዘለ እንጉርጉሮ ነው። አጻጻፉም በዕብራይስጡ አበገደ አካሄድ ነው። የዕብራይስጥ የፊደላቸው አኀዝ 22 ነውና ለዚህ ነው እያንዳንዱ ምዕራፍ በ22 ጥቅሶች የተከፈለው። ምዕራፍ ሦስት 66 መሆኑ 22 በ3 ተባዝቶ ነው። ይህ ራሱ አስገራሚ ስልትና በቃል ለመያዝ የሚረዳ አጻጻፍም ነው። ይህ መጽሐፍ ሲጠና ታሪካዊው ዐውድ ወይም የኢየሩሳሌም ጉስቁልናና የዘመኑ የአይሁድ ሁኔታ ፈጽሞ መታለፍ የለበትም። ኤርምያስ ኢየሩሳሌም በፈረሰችበት፥ መቅደሱ በወደመበትና ሕዝቡም በተጋዘበት በምርኮው ዘመን ያገለገለ ነቢይ ነው። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥም በርካታ የሙሾ ወይም የኀዘን መዝሙሮችን እናገኛለን፤ ለምሳሌ፥ መዝ. 31፤ 39፤ 137፤ 142።

መኃልይ ማለት ማኀሌት ወይም የምስጋና፥ የአድናቆት መዝሙር ማለት ነው። መኃልየ መኃልይ ሲልም መዝሙረ መዝሙራት ወይም ከመዝሙሮች የበለጠ መዝሙር ማለቱ ነው። መኃልየ መኃልይ የፍቅር መጽሐፍ ነው። ስለ ውበትና ስለ ፍቅር የሚናገር መጽሐፍ ነው። አንዳንድ መጻሕፍት አንድ የጎላ ጭብጥ አላቸው። ለምሳሌ፥ መዝሙረ ዳዊት አምልኮን፥ መጽሐፈ ምሳሌ ጥበብን ይገልጣሉ። በዚህ መጽሐፍ ደግሞ ውበትና ፍቅር፥ በፍቅርም የሚገኝ ደስታ ተገምደው ይገኛሉ። በፍቅር አንዱ ለሌላ ሙሉ ለሙሉ መሰጠት ተደጋግሞ ተወስቶአል። የፍቅር ኃይልም የጋለ፥ የበረታና የከበረ፥ እንዲሁ ለሰዎች የተሰጠ ሆኖ ቀርቦአል። ይህን መጽሐፍ በምሳሌያዊ አፈታት የሚፈቱ ሰባኪዎች ይህ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል፤ ደግሞም፥ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያንና መካከል ያለውን ፍቅር በምሳሌያዊ አቀራረብ ይወክላል ይላሉ። በእግዚአብሔርና በእስራኤል ወይም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ውብ ግንኙነት ቢኖርም በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ እንዳየነው የሚነበበው ክፍል ግልጽ ከሆነ እንዳለ መውሰድና ምሳሌያዊ ከሆነ ተጠንቅቆ መፍታት አግባብ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል። መኃልየ መኃልይ





በውስጡ በርካታ ተምሳሌቶችንና የስዕላዊ ቋንቋ መግለጫዎችን የያዘ ቢሆንም መጽሐፉ በሙሉው ግን ምሳሌያዊ መጽሐፍን አይመስልም። ከዚህ አንጻር በበርካታ አስተማሪዎች ተቀባይነት እንዳገኘው መጽሐፉ በቀጥታ በሰሎሞንና በሱላማጢስ ወይም በሱላማዊቷ ፍቅረኛው መካከል የታየ አካላዊ፥ ስሜታዊና ወሲባዊም የሆነ ንጹሕ ፍቅር ነው እንጂ ሌላ አይደለም። በምሳሌያዊ አፈታት ፈትተው የሚያስተምሩት ሰዎች እንዲህ ማድረጋቸው እንዲህ ያለው ፍቅር በጣሙን ምድራዊና ሥጋዊ በመሆኑ ይህን ለማጣጣልና እግዚአብሔር ይህን ምሳሌ አድርጎ ሰማያዊውን መና ገሩ እንደሆነ በማሰብ ነው። በቀጥተኛ አፈታት የሚያስተምሩት ደግሞ በዘፍጥረት መጽሐፍ እንደሚታየው እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ፍቅር ራሱ ፈጥሮ ባርኮታል፤ ይህ ፍቅር የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ የሚገለጠውም በጋብቻ ነው፤ ከኃጢአት በኋላ ሰው አበላሸው እንጂ። ደግሞም መጽሐፉ የሚያሳየው ፍቅርን በተለያዩ ደረጃዎች ሲያድግና ሲጠነክር፥ ዋጋ ሲያስከፍልና በመጨረሻም ሲያረካ ነው ይላሉ። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን እንደ ባልና ሚስት ወይም ሙሽራና ሙሽሪት ተደርገው ተጠቅሰዋል፤ ኤፌ. 5፤ ራእ. 19 ወዘተ። በእርግጥ ግንኙነቱ የእግዚአብሔርንና የሕዝቡን ወይም የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን በስሱ ሊመስል የሚችል ቢሆንም መጽሐፉን በጥሬው መውሰዱና በቀጥታ ማየቱ ጤናማው አፈታት ነው።

በስልቱ መኃልየ መኃልይ በዕብራይስጥ ግጥም የተጻፈ ሆኖ በጣም ገላጭ የሆኑ የፍቅር፥ የአካላዊ ውበትና የተፈጥሮ ቃላትን በብዛት ይጠቀማልና በዚህ ከሌሎች መጻሕፍት በጉልህ ይለያል። በመጽሐፉ ውስጥ ሦስት የተለያዩ ሰዎች ወይም ተናጋሪዎች ስለሚታዩ መጽሐፉ ቴአትር የመምሰል ዝንባሌም አለው። ወንዱና ሴትዋ ተናጋሪዎች ሁለቱ ሲሆኑ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት የተባሉት ሦስተኞቹ ይሆናሉ። አንዳንድ ሊቃውንት ባለ አምስት ወይም ስድስት ገቢር ቴአትር አድርገውም ይከፋፍሉታል።

ሦስቱን የመዝሙር መጻሕፍት በአጭሩ እንዲህ ከተመለከትን ቀጥሎ ደግሞ ሦስቱን የጥበብ መጻሕፍት እንይ። የጥበብ መጻሕፍት የሚባሉት ኢዮብ፥ ምሳሌና መክብብ ናቸው። የጥበብ መጻሕፍት ሲባልም በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ጥቅሶች በሙሉ የጥበብ ጥቅሶች ናቸው ወይም ስለ ጥበብ ይናገራሉ ማለት ሳይሆን መጻሕፍቱ በአጠቃላይ የጥበብ ይዘት አላቸው ማለት ነው። እውቀትን ከሕይወት ጋር በማዛመድ የሚኖሩበት ጥበብ ከውስጣቸው ይገኛል። እነዚህ የጥበብ መጻሕፍት የተለያዩ ሰዎች ሕይወትን የገለጡበት መጻሕፍት ናቸው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ጠይቀውም ሆነ ሳይጠይቁ ጥበብን የተለገሱ በርካታ ሰዎች እናገኛለን። የእነዚህ ሰዎች ምክሮች ይደመጡና ይኖርባቸውም ነበር። ነገሥታትም ሳይቀር እንዲህ ያሉ ሰዎችን ለምክር ይፈልጉአቸው ነበር። በጥበብ መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው

እንደዚህ ያሉ ሰዎች የተረዱትን ጥበብ በአእምሮ ከማወቅ አልፎ በልብ ስለ መረዳትና በሕይወትም ስለ መኖር ሲሉ ለሌሎች ያስተላለፉት እውነት ነው። የተጻፈው ቃል በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው። ሆኖም መስተዋል ያለበት ፍሬ ነገር በውስጡ የምናገኛቸው ሰዎች ለሕይወት ያላቸው አመለካከት ትክክለኛና ቃላቸውም በሙሉ ምንም ስሕተት የሌለበት ነው ማለት አለመሆኑ ነው። ለምሳሌ÷ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ከሙሉው መጽሐፍ አንጻር የምናያቸው አምስት ሰዎች÷ ወይም በመክብብ የምናገኘው ሰባኪ ስለ ምድራዊ ሕይወት ያላቸው አመለካከት ፍጹምና ምሉዕ አይደለም። ሰዎቹ ጠቢባን ናቸው ማለትም የግድ መንፈሳዊ ናቸው ማለት አይደለም። ከኢዮብና በትንሹ ከሰባኪው በቀር ስለሌሎቹ የምናገኘው መረጃ ነገር የለም። ሰባኪው ሰሎሞንም ጠቢብ ቢሆንም ጥበቡ ከእግዚአብሔር እንዳይርቅ አላገደውም። ትምህርቶቹ እንግዲህ መንፈሳዊ እውነቶች ያሉባቸው ቢሆኑም መንፈሳዊ ብቻ አይደሉም። በውስጣቸውም መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ÷ ቤተ ሰባዊ÷ ግላዊ÷ አስተዳደራዊ÷ ምጣኔ ሀብታዊ÷ ነገሮችም አሉበት። በአጠቃላይ ከዕለታዊ ኑሮና ትግል ጋር የተቀራኙ ምክሮች ናቸው እንጂ ጠሊቅ ትምህርት የተንጸባረቀባቸው አስተምህሮቶች ወይም ትእዛዛትም አይደሉም። ምክሮቹና ንግግሮቹ የያዙት ቁም ነገርም ውሱን ሆኖ እንደ ተናጋሪዎቹ እውቀት መጠን ይለያያል። ኤልፋዝ ያለው እውቀት ውሱን ነው፤ የሚያውቀውን ያን ውሱን ነገር ነው ሲናገር የምናነብበው። ልሙኤልም÷ ሰሎሞንም÷ ሌሎቹም እንዲሁ በደረሱበትና በተረዱት ያገኙትን ተግባራዊ ምክር ነው የሚናገሩት። ሆኖም የነዚህ ሁሉ ሰዎች ውሱን እውቀት ውሱን ከሆነው ባሻገር ያለውን እንድንፈልግና እንድናውቅ ሲባል እንዲጻፍልን እግዚአብሔር አድርጎአል።

መጽሐፈ መክብብ የአንድ ፈላስፋ የሕይወት ርዕዮት ነው። መጽሐፉ ምንም እንኳ አልፎ አልፎ አንዳንድ ምክር ቢለግስም በአጠቃላይ ሲታይ አሉታዊና ጸለምተኛ የሕይወት ፍልስፍናን የያዘ መጽሐፍ ይመስላል። ሁሉ ከንቱ ነው፤ ሞት አይቀሬ ነው፤ ከሞት በኋላ መታሰብ የለም፤ ስለዚህ ሁሉ ድካም ነው÷ ከንቱ ድካም፤ ዋጋቢስ። ይህ ነው ሰፊ መልእክቱ። ተስፋ አስቆራጭ መጽሐፍ ይመስላል። እንዲያውም ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጋር የሚጋጭ ይመስላል። እግዚአብሔርንም በየዕለቱ ካለን ኑሮ ጋር ጉዳይ የሌለውና የማይገደው ያስመስለዋል። እንዲህ ከሆነ ስለምን ተጻፈ? የተጻፈበት ዋና አሳብም ይኸው ራሱ ነው። ማለትም÷ የሰውን ፍልስፍና ከእግዚአብሔር አሳብ አንጻር ማየትና መረዳት እንችል ዘንድ ነው። የእግዚአብሔር ፍርሃት የሌለበት ነገር ምንም ሙሉ ቢመስልና ቢሆንም ከንቱ ነው። የመጽሐፉ አጨራረስም ወደዚህ ድምዳሜ የሚያመለክት ነው። የመጽሐፉ አደማደም ከራሱ ከመጽሐፉ ውስጥ ወጥተን እግዚአብሔርን የምናውቅበትንና የምንፈራበትን ቃሉንና ትእዛዙን እንድንፈልግ የሚጋብዝና የሚጠራ ነው። መጽሐፉ ጸለምተኛ ይምሰል እንጂ አለመሆኑ የሚታየውም





እዚህ ላይ ነው። ትእዛዙን ጠብቅ ብሎ ከጨረሰ÷ ትእዛዙ የቱ ነው ብለን እንድንጠይቅና ወደዚያ እንድናመራ የሚያመለክት ጠቋሚ ነው። አመልካች መጽሐፍ ነው። እዚህ ችግር ነው፤ መከራ ነው፤ ከንቱ ነው፤ እዚያ ግን ሕይወት ነው፤ ትርጉም አለ፤ ብሎ ወደ ሕት መጽሐፍና ወደ ሕት ጌታ የሚያመለክት ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ይህን መጽሐፍ ካነበበና ምክሩን ከተቀበለ ቀጣዩ እርምጃው ሕጉንና እርሱን መፈለግና ለእርሱ መገዛት ነው።

መጽሐፈ ኢዮብንም በጥቅሉ ስንመለከት እንደ መጽሐፈ መክብብ የሰዎችን አመለካከትና ከዚህም የተነሣ ትክክለኛ ያልሆኑ ድምዳሜዎቻቸውን የምናገኝበት መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ መጨረሻ ክፍል ግን የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ዕቅድና የኋለኛ አሳብም ስለምናይ እንደ መጽሐፈ መክብብ አጨራረሱ ትክክለኛ ሆኖ እናያለን እንጂ የኢዮብም ሆነ የአጽናኞቹ ሁሉ አመለካከትም÷ የሕይወት ግምጋሜም÷ ድምዳሜም የተሳሳተ ነበር። በመጽሐፉ ውስጥ የምናገኘው የሰዎቹ ፍልስፍና ወይም እምነት ሰው መልካም ከሆነና ካደረገ ከእግዚአብሔር በጎነት ይሆንለታል፤ ከከፋና ከበደለ ግን መከራና ቅጣት ታገኘዋለች የሚል ነው። በኢዮብም ላይ የሚያቀርቡት ክስና ውንጀላ÷ 'ይህ ያገኘህ ክፉ አድርገህና በድለህ÷ ከእግዚአብሔርም ተጣልተህ ነውና ተናዘዝ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር ታረቅ' የሚል ዓይነት ነው። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ለዘመናት የኖረ ነው። በዮሐ. 9 እንደምናገኘው የጌታ ደቀ መዛሙርትም ያ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን መሆኑን ጠይቀው ነበር። መከራ ሁሉ የኃጢአት ውጤት ነው ብለው ይቀበሉ ስለነበር ነው እንዲህ ያሰቡትና የጠየቁት። ይህ አመለካከት÷ ማለትም÷ የወላጆች በደል በልጆች የሚያመጣው ዋጋ አስከፋይነት ዛሬም በክርስቲያኖችም ጭምር ዘንድ ያለ አመለካከት ነው። ይህንን በሌላ ገጽ እናየዋለን። ይህ ግን ልክ ያልሆነ አመለካከት ነው። በእርግጥ ስሜታዊው÷ ልቡናዊውና አካላዊው ገፈት የሚያገኘን ቢሆንም በመንፈሳዊው ረገድ አዲስ ፍጥረት ስንሆን አዲስ ተፈጠርን እንጂ አልተጠገንንም።

ወደ ኢዮብ መጽሐፍና ወደራሳችንም ስንመለስ ያለነው በወደቀች ምድርና በሰይጣን ሥርዓት ስር ባለ ግዛት ነው። ስለዚህ÷ አንደኛ÷ ሰው በግሉ ባላደረገው መከራ ውስጥም ተካፋይ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዘመን ሰው ብቻ ሳይሆን ለከንቱነት የተገዛ ፍጥረትም ሁሉ በመቃተት እንደሚኖር ቃሉ አስረግጦ ይናገራል። ሁለተኛም÷ በእግዚአብሔር ፈቃድም በቅዱሳን ላይ መከራ ሊመጣ ይችላል። ይህም የሚሆነው ለምክንያት ነው፤ ለዓላማ÷ ለግብ÷ ለበጎ። ኢዮብ ራሱ የዚህ ምሳሌ ነው። በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ኢዮብ ራሱም ያልተረዳውን ነገር እኛ አንባቢዎቹ እንረዳለን። ያም ከመጋረጃው ጀርባ ምን እየሆነ እንዳለ ኢዮብ አላወቀም፤ እኛ ግን ተጽፎልን እያነበብን ነንና ይህን አውቀናል። ስለዚህ በኢዮብ ላይ የሆነው ሁሉ በፍጹም መለኮታዊ ፈቃድ መሆኑን

እንገነዘባለን። አንዳንድ የቃል-እምነት ሰባኪዎች በኢዮ. 3፥25 ያለውን 'የፈራሁት' እና 'የደነገጥሁበት' የሚሉትን ቃላት ከጥቅሱ ነቅሎ በመውሰድ በኢዮብ የደረሰው ሁሉ ኢዮብ ቀድሞውኑ ይመጣብኛል፥ ይደርስብኛል እያለ ይፈራና ይናገር ስለነበረ ነው፤ በቃሉ ስለተናገረ ነው የደረሰበት፤ እኛም የምንናገረው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ነገር ሁሉ ይደርስብናል ወይም ይደርስልናል ይላሉ። ይህ ቃልን ብቻ ከጥቅሱ ውስጥ የማውጣትና ዐውድን እንደሌለ የመቁጠር ስሕተት ነው። ደግሞም ይህ የ 'ተናገር ይሆንልሃል፥ ተናገር ይሆንብሃል' አባባል ውኃ የማያነሣ መሆኑን ከኢዮብ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ብቻ እንኳ እናገኛለን። አባባሉም ሁሌም እውነትን ተከትሎ አይሄድም። አንድ ብቻ ምሳሌ ለመውሰድ፥ ጌታችን ስለ መስቀል ሞቱ ደጋግሞ ተና ግሮአልና የሞተው ስለተናገረ ነው ልንል ነው? ወይም ያን ባይና ገር ኖሮ አይሞትም ልንል ነው? ከዐውድ መውጣት ማለት እንዲህ እንዲህ ነው።

በመጽሐፈ ኢዮብ የምናገኘው ትክክለኛ ጥበብ ከኢዮብ 38፥1 እስከ 42፥6 ያለው ክፍል ነው። ከዚያ የቀረው በሰዎች እይታ የታየ ጥበብ ነው። በውስጡ እውነቶች አሉ። የተሳሳቱ አመለካከቶችም አሉ። ኢዮብ ጽድቁን ወይም ትክክለኛነቱን ሲናገር ሦስቱ ወዳጆቹ እግዚአብሔርን እንደሚሳደብ አድርገው ቆጠሩት እንጂ አልተረዱትም። ከሦስቱ ቀጥሎ የመጣው አራተኛው ከሌሎቹ ትንሽ የተሻለ ምላሽ ነበረው። ከሁሉም በኋላ ግን እግዚአብሔር ራሱ ተገልጦ መልስ ሰጠ። ስሕተትንም ጥበብንም ገለጠ። የኢዮብም ሆነ የወዳጆቹ አመለካከት ተገለጠ፤ ኢዮብ ጸደቀ፤ የሆነው እንዲሆን ቢፈቅድ እግዚአብሔር የማይጠየቅ ባለ ሥልጣን መሆኑ ታወጀ። የመጽሐፈ ኢዮብ ዋና ግብ በሕይወት የሚደርሰው ነገር ሁሉ መልካም ላይሆን እንደሚችል፥ ደጎችም ክፉ ሊያገኛቸው እንደሚችልና የሆነው ስለሆነ ደግሞ እግዚአብሔር ሊወቀስ እንደማይገባው፥ የሆነው ሁሉ ያለእርሱ ፈቃድ እንድዳልሆነም ማስተማር ነው።

መጽሐፈ ምሳሌ የጠቢባን ምክር መጽሐፍ ነው። በአብዛኛው የጠቢቡ የሰሎሞን ቃላት ቢሆኑም አጉርንና ልሙኤልን ጨምሮ ሌሎች ጠቢባንም የሰጡት የምክር ቃላት እንዳሉበት ተጽፎአል፤ ምሳ. 30፥1፤ 31፥1 እና 24፥23። ምክሮቹም በጣም ተግባራዊ ከሆኑ ዕለታዊ የኑሮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። ልክ ወላጆች ለልጆች ማኅበራዊ ትሳትፎአቸው ጤናማ፥ ከመንግሥት ጋር የማይጋጩ፥ በትዳራቸው ጨዋ፥ በግል ሕይወታቸው ትጉህና ታታሪ ሠራተኞች እንዲሆኑ የሚሰጡትን ምክር ይመስላሉ። በአንድ በኩልም ናቸው። ማጋጣዎችና ሰነፎች፥ ሰካራሞችና ቃል አፍራሾች እንዳይሆኑ፥ ከክፉ ባልንጀሮችና ከመጥፎ ሴቶች እንዲጠበቁ የሚመክር ነው። ከወንጀል እንዲርቁ፥ ከችኮላ ውሳኔ እንዲጠበቁ፥





ለራስ ከመስነፍ፥ ሌላውን ከማታለልና ከዝሙት እንዲርቁ በስፋት ይመክራሉ፤ መምክር ብቻም ሳይሆን እነዚህ ነገሮች የኋላ ኋላ መዘዝ እንደሚያኖራቸውም በማሳወቅ ያስጠነቅቃሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖር ግንኙነት ጠንቃቃ ስለመሆን፥ ወላጆችን ስለማክበር፥ ልጆችን ስለመቅጣት፥ አዛውንትን ስለመስማት፥ መሪዎችን ስለማክበር፥ እግዚአብሔርን ስለመፍራት በግልጽ ይናገራሉ። እነዚህ የጠቢባን ምክሮች ቢደመጡ ውጤት የሚያመጡ ምክሮችና እዝናት ናቸው፤ ሆኖም ዋስትናዎች ወይም ከእግዚአብሔር በቀጥታ የተሰጡ ትእዛዛትና ተስፋዎች አይደሉም። ምክሩ በአመዛኙ በወጣት ዕድሜ ያሉት ላይ ያተኩራል። ወደ ሙሉ ዕድሜ ደርሰው ሕይወታቸውን ወደ ኋላ ዘወር ብለው ሲያዩ ምንም ቅር የማይሰኙ የተሳካላቸው ሰዎች እንዲሆኑ ይረዳል። ስለዚህ መጽሐፈ ምሳሌን ስናጠናም ሆነ ስንፈታ ተገቢ ጥንቃቄ ያሻናል።

በመጽሐፍ ምሳሌ ውስጥ ያሉት ምሳሌዎች አጻጻፍ በሃይማኖታዊ ቋንቋ አይደለም። ምክር የግድ በሃይማኖታዊ ቋንቋ ማሸብረቅ የለበትም። የተጻፉት ምሳሌዎች ኀብር ያላቸው አጫጭር ቁም ነገሮች ናቸው። ንግግራቸውም ፈሊጣዊ ነው። ልክ እንደ አገራችን ምሳሌዎች ናቸው። በዕብራይስጥ ማሻል מָשָׁל ማለት ምሳሌ ማለት ነው። መጽሐፈ ምሳሌ ሚሻሊም ነው የተባለው፤ ምሳሌዎች ማለት ነው። ዓላማቸውም ከላይ እንደተመለከትነው ምክር ነው። ምክሮቹም ምክሮችና በአጠቃላይ ሲታዩ እውነትነት ያላቸው ንግግሮች ናቸው እንጂ ትእዛዛት አይደሉም። አጠቃላይ እውነትነት ሲባልም ሁልጊዜና በሁሉ ቦታ እውነት ላይሆኑም ይችላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ በምሳ. 16፥7 ላይ የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ካሰኘ በእርሱና በጠላቶቹ መካከል እንኳ ሰላም እንደሚሆን ይናገራል። ይህ አጠቃላይ እውነታን የያዘ አባባል ነው፤ ሁሌም እውነት ይሆናል ማለት ግን አይደለም። ሁሌም እውነት ቢሆን ክርስቶስ ከቶ ጠላቶች ባልኖሩትና ባልሰቀሉትም ነበር። በታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ሰማዕታትም በሰማዕትነት ባላለፉ ነበር። በአጠቃላይ ክርስቲያኖች ሁሉ ምንም ጠላት ባልኖራቸው ነበር፤ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን መሥርተዋልና። እውነቱ ግን ክርስቶስ ወይም ክርስቲያኖች ጠላቶቻቸውን ቢወዱም በጠላቶቻቸው ግን አልተወደዱም። በምሳ. 14፥13 ደግሞ በሳቅ ልብ እንደሚያዝንና የደስታ ፍጻሜ ልቅሶ እንደሆነ ይናገራል። ይህ አንዳንዴ ሊሆን የሚችል ነገር ነው፤ ሁሌም በሳቅ ልብ አያዝንም።

የቃል-እምነት ሰባኪዎች ምሳሌ 6፥2ን በመጥቀስ በቃላችን የምንናገረው ነገር ይደርስልናል ወይም ይደርስብናል ብለው አጠንክረው ያስተምራሉ። ከላይ ካየነው ከኢዮ. 3፥25 ጋርም ያያይዙታል። ይህ ግን ከጥቅሱ አሳብ የራቀ ትምህርት መሆኑን ከዐውዱ እናገኛለን። የምሳ. 6፥2 የቅርብ ዐውድ ከቁጥር 1 እስከ

5 ያለው ክፍል ነው። ይህ ክፍል ለጎረቤት ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን እጅን አጋና መምታት ወይም ጽኑ ቃል መግባት ራስን ተያዥ ማድረግ መሆኑንና ዕዳውን ያ ሰው ካልከፈለ ተያዥ ወይም ዋስ የሆነው እንደሚከፍል መናገሩ ነው። ይህ ከመናገር ይልቅ የዋስትና ጉዳይ ነው። ዋስትና ደግሞ በቃል ነው የሚገለጠው። እንግዲህ ለዚህ ነው ምክሮችን ከእግዚአብሔር እንደተሰጡ ተስፋዎች ወይም ትእዛዛት ሳይሆን፥ ዋና አስተምህሮት የሚመሠረትባቸው መሠረቶችም አድርገን ሳይሆን እንደ ምክርነታቸው መቀበል ያለብን። እነዚህን ምክሮች ብናደርጋቸው እንጠቀማለን፤ ባናደርጋቸው ጥቅም ይቀርብናል ወይም ጉዳት ያገኘናል። በመጽሐፉ ውስጥ የምናገኛቸው በርካታ ምክሮች ለስኬታማ ኑሮ ምክሮች እንጂ ዋስትናዎች አይደሉም።

የምሳሌ አጻጻፍ ስልት ምሳሌያዊና ግጥማዊ መሆኑም መዘንጋት የለበትም። ምሳሌ አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር በመመሰል፥ በማነጻጸርና በማወዳደር መናገርን በብዛት ይጠቀማል። ለምሳሌ ከአልጋው የማይነሣ ታካች በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር ሳንቃ፥ በሌላው ጥል የሚደባለቅ ውሻን በጅራቱ እንደሚይዝ ተመስለዋል። እንደየትኛውም ባህል ምሳሌ ሁሉ በቃልና በልብ እንዲያዙ ሆነው ነው የተሠሩት። አጫጭርና በድምጽ ወይም በምስል በአእምሮ ሊቀረጹ ተብለው የተሠሩ ናቸው። ምሳሌዎች በነጠላ ሊወሰዱ የሚችሉ ትናንሽ ክፍሎች ናቸው። ሆኖም የጠቅላላው መጽሐፍ አሳብ፥ ማለትም፥ ለስኬታማ ኑሮ የተሰጡ ምክሮች ስብስብ መሆኑ እንዲሁም ዋናው ስዕል፥ ማለትም፥ የጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አብረው መታየት አለባቸው። አንድ የምሳሌ ክፍል ወይም ተመሳሳይ አሳብ ያላቸው ምሳሌዎች ተወስደው ሲጠኑ ያ አሳብ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእንዴት እንደቀረበ መጤን አለበት።

ከላይ እንደተመለከትነው በአጠቃላይ የጥበብ መጻሕፍት በአጻጻፋቸው የተለያዩ ናቸው። ኢዮብ የንግግሮች ስብስብ ነው። ምሳሌ የምሳሌዎች ስብስብ ነው። መክብብ የአንድ ሰው ስብከት ወይም ጥናታዊ ንግግር ነው። የጠቢባኑ ንግግር ወይም ትምህርት በእውቀታቸውና በልምዳቸው ላይ የተመሠረተ ሆኖ አጻጻፋቸው በአብዛኛው በዕብራይስጥ ግጥም ነው። እንዲህ ያለው አጻጻፍ ከስድ ንባብ ይልቅ በቀላሉ በቃል ለመያዝ አመቺ ነው። ደጋግመን እንዳየነው እነዚህ መጻሕፍት በእየራሳቸው ሙሉ መጻሕፍት በመሆናቸው ሙሉው ዐውድ ሳይዘነጋ ያለአግባብ ከመሰባበር በአግባብ መበለት ተገቢ ነው። በመጽሐፉ ምሳሌና መክብብ ውስጥ የምናገኛቸው በርካታ ምሳሌዎችና የሰባኪው ቃላት በነጠላ ወይም በስብስብ የሚወሰዱ ናቸው። እንዲህ ሲደረግም የቅርብም ሆነ ጠቅላላ ዐውዱ ሳይዘነጋ መሆን አለበት።





# የትንቢት መጻሕፍት

የነቢያት መጻሕፍት አሥራ ስድስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የያዘ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። በብሉይ ኪዳን የዓይነት ስብስቦች ውስጥ ከሁሉም ይበልጥ ብዙ መጻሕፍት የያዘው ክፍል ይህ ነው። በአይሁድ ወይም የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በእኛው መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ብሉይ ኪዳን ተራ ተከተል የሚሄድ ሳይሆን በሦስት ቦታዎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ቶራ ወይም ኦሪት፤ ሁለተኛው ነቢኢም ወይም ነቢያት፤ ሦስተኛው ኬቱቢም ወይም ኪታቦች ወይም ጽሑፎች ተብለው ተከፍለዋል። ጽሑፎች የታሪክ፥ የቅኔና የጥበብ መጻሕፍትን ሁሉ ያቅፋሉና በዕብራይስጡ አቀማመጥ ትልቁ ስብስብ የጽሑፎች ስብስብ ነው። የነቢያት መጻሕፍት በእነርሱ በመካከል የሚገኙት ሲሆኑ በእኛው በብሉይ መጨረሻ ይገኛሉ። የብዙ ትንቢቶች ፍጻሜ እንደሆነ የሚታየው አዲስ ኪዳን ከእነርሱ ቀጥሎ እንዲገኝ በማሰብ የተደራጀ አቀማመጥ ይመስላል።

የትንቢት መጻሕፍትን ለመረዳት በመጀመሪያ የትንቢትን ምንነት ማወቅ ተገቢ ነው። ብዙውን ጊዜ ትንቢትን በአንድ ገጽታው ብቻ እናውቀዋለን። ያም ትንቢት ወደፊት የሚሆነውን ነገር እንደሚናገር ቃል መሆኑን ነው። በእርግጥም ትንቢት በእግዚአብሔር ምሪት ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚናገር ቃልም ነው። ወደፊት የሚሆነው ነገር ወይም ትንቢት ድርብ ግብ አለው። ያም የመጀመሪያው፥ ትንቢቱን የሚሰሙትን ሰዎች ሕይወት መንካትና በኑሮአቸው ወይም በሕይወታቸው ላይ ለውጥ መፍጠር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ያ የተነገረው ነገር ሲፈጸም ቃሉን በላከውና በፈጸመው ጌታ ላይ የሚደረገው መታመን ነው።

ስለሆነም የወደፊቱን ነገር መናገር ብቻውን ትንቢት ለሚለው ቃል ከፊል ትርጉሙ ነው እንጂ ብቻውን ሙሉው አይደለም። ሌላው የትንቢት ገጽታ የሚመጣውን ብቻ ሳይሆን ያለፈውንና አሁንም ያለውን በመግለጥ የእግዚአብሔርን አሳብ ማሳወቅ ነው። በግሪክ ቋንቋ ትንቢት የሚለው ቃል ፕሮፌቴያ *(προφετεία)* ይሰኛል። ከሁለት ቃላት የተሠራ ነው። ፕሮ *(προ)* የሚለው ወደ ፊት ለፊት ወይም ወደ ግልጥ ማምጣትን፥ ማውጣትን ወይም መግለጥን የሚያመለክት ሲሆን፥ ሁለተኛው የቃሉ ክፍል ፌሚ *(φημί)* ደግሞ መናገር ማለት ነው። በአንድነት ሲቆራኙ ትንቢት ማለት ወደፊት አምጥቶ ወይም ገልጦ መናገር ማለት ነው። የቃሉ ጥሬ ትርጉም ወደ ፊት የሚሆነውን ከመናገር ይልቅ የሆነውን ወይም እየሆነ ያለውን ገልጦ መናገርን የያዘ ነው። ይሁን እንጂ ትንቢት ሁለቱንም አሳቦች አጣምሮ የያዘ መሆኑን፥ ማለትም፥ ወደ ፊት የሚሆነውን መናገርንም፥ ያለፈውንና የጊዜውን ነገር በመናገር መለኮታዊ አሳብን መግለጥ መሆኑንም መረዳት ተገቢ ነው።

በትንቢት መጻሕፍትም ሁለቱንም አሳቦች ነው በስፋት የምናገኘው። ወደ ፊት የሚሆነውን ከሚናገረው ትርጉም አንጻር ስናየው ወደ ፊት የሚሆነውን ከተነበዩት አብዛኛዎቹ ትንቢቶች በተነገሩ በአጭር ጊዜ የተፈጸሙ ናቸው። እጅግ ብዙዎቹ ትንቢቶች ስለ ዘመናቸውና ስለ ሕዝባቸው፥ እንዲሁም ተጎራብተዋቸው ለኖሩት አሕዛብ የተነገሩ ነበሩ። ትንቢቶቹ በተነገሩበት በዚያ ዘመን ለነቢያቱና ለተቀባዮቹ ጊዜው ገና ትንቢታዊ ቢሆንም ለእኛ አሁን ላለነው ግን ያለፈ ታሪክ ነው። አሁን ከዚህ ዘመን አንጻር ስናያቸው ተፈጽመው ያበቁ ትንቢቶች ናቸውና ገና ወደፊት እንደሚፈጸሙ ትንቢቶች አናያቸውም። አንዳንድ ሰዎች የትንቢት መጻሕፍት በሙሉ ስለ አዲሱ ኪዳንና ስለ መሢሑ እንዲሁም ገና ከአሁን በኋላ ስለሚመጣው ነገር የሚናገሩ ይመስላቸዋል። የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት እንደሚናገሩት በጣም የሚያስገርመው ነገር ስለ እነዚህ ጉዳዮች የሚያወሱት የትንቢት መጻሕፍት ክፍል ከአሥር በመቶ ያነሱ ናቸው፤ ገና ከዚህ ወደፊት የሚሆነውን የሚናገሩት ደግሞ ከዚያም በጣም፥ በጣም ያነሱ ናቸው። ሆኖም የተፈጸሙ ብቻ ሳይሆኑ፥ ቁጥራቸው ቢያንስም እንኳ ገና ወደፊት የሚፈጸሙ ትንቢቶችም በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ።

እንግዲህ ነቢያት የእግዚአብሔርን አሳብ ለዘመናቸው ሰዎች የሚናገሩ መልእክተኞች ናቸው። ይህ ዋና አገልግሎታቸው ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ከካህናት ጋር ሲነጻጸሩ ካህናት የሰውን በደል ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ ወይም ስለ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ነቢያት ግን የእግዚአብሔርን አሳብ ለሰዎች አቅራቢ ናቸው። ስለዚህም ነው በነቢያት መጻሕፍት ይዘት ውስጥ ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ምክርን፥ ተግሳጽን፥ ትምህርትን፥ አንዳንዴም ታሪክን ወይም ትረካን የምናገኘው። የአንዳንዶቹን ነቢያት ታሪክና ሥራ፥ ለምሳሌ፥ ኤልያስ፥ ኤልሳዕ፥ ናታን፥ ሕልዳና ወዘተ፥ በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ አናገኝም። በአንጻሩ ደግሞ በትንቢት መጻሕፍት የምናገኛቸውን ነቢያት የሕይወት ታሪክ በትንቢት መጻሕፍቱም ሆነ በሌሎች የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ውስጥም አናገኝም። በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ እንዲጻፉ እግዚአብሔር ያደረገው ተፈላጊውንና አስፈላጊውን ብቻ ነውና።

አንዳንድ የትንቢት መጻሕፍት አንድ ወጥ ወይም በአንድ ዒላማ ላይ የተነጣጠሩ ናቸው፤ ለምሳሌ፥ ትንቢተ ዕንባቆም፥ ትንቢተ ዮናስ፥ ወዘተ። አብዛኞቹ ግን የተለያዩ ትንቢቶች ስብጥርና ስብስብ ናቸው። ስለዚህም ምንነታቸውን ለመረዳት ዐውዱ እንዳለ ሆኖ የግድ ተነጣጥለው ወይም ተከፋፍለው መታየት አለባቸው። አንዳንዶቹ የትንቢት መጻሕፍት ግን ድንበራቸው በቀላሉ የሚገኝ ባለመሆኑ እንደ ሌሎቹ የመጻሕፍት ዓይነት ቶሎ ለመከፈል የሚያመቹ አይደሉም። ስለዚህ ጥንቃቄ የተመላው ጠሊቅ ጥናት ይጠይቃል። በትንቢት መጻሕፍት ጥናት ጥንቃቄ የሚሻ ሌላ ነጥብ እኛ አንባቢዎቹ ነቢያቱ ከኖሩበትና ከተነበዩበት





ዘመን በጣም የራቅን በመሆናችን እንደ ተነባቢ ለመጀመሪያዎቹ የቃሉ ተቀባዮች በቀላሉ የሚገቡት ነገሮች ለእኛ የማይገቡን መሆናቸው ነው። ርቀታችን በዘመን ብቻ ሳይሆን በመልክዓ ምድር፥ በባህል፥ በሃይማኖትም ጭምር በመሆኑ በርካታ እንግዳ የሚሆኑብን ነገሮች ይኖራሉ።

እነዚህን ነገሮች አልፈን መረዳት እንድንችል የነቢያቱን ማንነትና የመልእክታቸውን ምንነት ማወቅ አለብን። ማንነት ሲባልም በነጠላ ነቢያቱ ማን መሆናቸውን፥ ማለትም፥ ለምሳሌ፥ ሕዝቅኤል ወይም ሆሴዕ ማን መሆናቸውን ማለት አይደለም። ለጠሊቅ ትንታኔ ይህን ማወቁ መልካም ነገር ነው። ግን እዚህ ላይ ማንነት ሲባል በአጠቃላይ ነቢያት ምን መሆናቸው ነው። ነቢያት በጥቅሉ ሕግ አስጠባቂዎች ወይም አስከባሪዎች ናቸው ማለት ይቻላል። ሕግ ሲባልም ሕገ ኦሪት ነው። ሕገ ኦሪት እንዲያው ዝም ተብሎ የተሰጠ ሳይሆን እስራኤል እንደ ሕዝብ እንዲጠብቁትና እንዲታዘዙት የተሰጠ ነው። ሕጉም ቢጠብቁት በረከት፥ ቢጥሉት ደግሞ እርግማን ታስረውበታል፤ ዘሌ. 26፤ ዘዳ. 4 እና 28። ሕጉ እንደተሰጣቸው መጠን እስራኤል ታዛዥና ታማኝ ሆነው ቢገኙ እነዚያ በረከቶች እንደ ሕዝብ የሚባረኩባቸው በረከቶች ናቸው። ቢታዘዙ በጤና፥ በምርት፥ በመፈራት፥ በድል አድራጊነትና በአሸናፊነት፥ በሰላም ተዘልሎ በመኖር፥ ወዘተ፥ ሊባረኩ ባይታዘዙ ደግሞ ከበረከቶቹ መቅረት ባሻገር በድርቅ፥ በበሽታ፥ በረኃብ፥ በወረራ፥ በግዞት ወዘተ፥ መከራ እንደሚቀበሉ ተነግሮአቸዋል። ቀደም ሲል በሕገ ኦሪት ትርጓሜ ክፍል እንዳየነው እነዚህ ሕግጋት ብሔራዊ ናቸው እንጂ ግለሰባዊ አይደሉም። ብሔራዊነታቸውም ለብሉይ ኪዳን እስራኤል እንዲሁም ያኔ እግዚአብሔርን በመፈለግ ወደ ይሁዲነት ይገቡ ለነበሩት ሁሉ ነው።

ከታሪክ መጻሕፍት እንደምንረዳው እስራኤል ብዙም ሳይቆዩ በዚህ ሕግ መኖርን ዘነጉ። እንደመሰላቸው መሄድና በፊታቸው መልካም የመሰላቸውን ማድረግም ጀመሩ። ከዚህም በላይ መለኮታዊ የሆነ ሕግ እያላቸው ከእግዚአብሔር ሕግና ከአሳቡ ርቀው በዙሪያቸው እንዳሉ አሕዛብ መኖርም ጀመሩ። በነዚህ ጊዜያት ነው እግዚአብሔር የተለያዩ መሪዎችንና ነቢያትን እያስነሣ መልካሙ እንዲበረታታና ክፉውን ለመገሰጽ እንዲያገለግሉና እስራኤል ወደ ቀደመው ቃል ኪዳንና ወደ ሕጉ እንዲመለሱ ማድረግ የጀመረው። ስለዚህም ነው ነቢያት የሕግ አስከባሪዎች የተሰኙት። የነቢያት ቃል ሕጉን ፹መመርኮዝ የተሰጠ የተግሳጽ ወይም የማበረታቻ ቃል ነው እንጂ ራሱ ሕግ አይደለም። ሆኖም ምንጩ እግዚአብሔር ነው እንጂ በጥበብ መጻሕፍት እንደምናገኘው ከሰዎች የመነጨ ንግግር አይደለም። ስለዚህም ነው በነቢያት መጻሕፍት ‘ይላል እግዚአብሔር’ የሚለውን ሐረግ እንደ አዝማች እጅግ ተደጋግሞ የምናገኘው። ነቢያት የመሰላቸውንና ለስሜታቸው የተሰማቸውን

አይናገሩም። እንዲህም ሆኖ ግን ቀድሞ በሙሴ አማካይነት ከተሰጠው ላይ የሚጨምሩት አንዳች የለም።

የነቢያት መጻሕፍት በጠቅላላ 16 ሲሆኑ ሁሉም ከ760 እስከ 460 ዓመተ ዓለም ባሉት 300 ዓመታት ውስጥ የተነገሩና የተጻፉ ናቸው። የመጀመሪያው አሞጽ የመጨረሻው ሚልክያስ ናቸው። የነቢያት አገልግሎት ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ቢኖርም በእነዚህ 300 ዓመታት ልዩ ልዩ ሕዝባዊ፥ ፖለቲካዊ፥ መንፈሳዊና ዓለማዊ እንቅስቃሴዎች ነበሩና ሕጉና የማሳሰቢያ ቃሉም እንደገና መታወስ አስፈለጋቸው። ኃጢአት እየበዛ፥ ሕዝቡም ከአምላኩ እየራቀ ሄዶ ቅጣት በደጅ የነበረበትና ወደ ቤትም የገባበት ዘመን ነበር። ማስጠንቀቂያ ተሰጠ፥ ቅጣት ተከተለ፤ ወደ ምርኮ ተጋዙ፥ ከዚያም የተወሰኑት ተመለሱ፤ የተመለሱት ደግሞ የመጽናኛ ቃል ያስፈልጋቸው ነበር። ስለዚህ ነው የነቢያት መጻሕፍት በነዚህ 300 የውክቢያ ዘመናት ውስጥ የተከማቹት።

ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጋር ሲነጻጸሩ ከትንቢት መጻሕፍት ጥቂቶቹ ለመረዳት የሚከብዱ ናቸው። አንዳንድ መጻሕፍት በጣም ግልጽና በጠረጴዛ ላይ እንደቀረበ ምግብ ያህል ለመበላት የተሰናዱ ናቸው። አንዳንዶች ግን የሰው ውሱን አእምሮ አሟልቶ ሊረዳቸው የማይችላቸው የእግዚአብሔር አሳቦች ናቸውና ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ፥ ትእግሥትና ጥናት ይጠይቃሉ። የጥናት መርጃዎችን ማማከርም ታሪካዊና ሌሎች ዳራዎችን እንድንረዳ በማድረግ ይበልጥ ያግዙናል። ጠቅላላ ዳራውን ስንረዳ ነጠላ ክፍሎችን በቀላሉ መረዳት እንችላለን።

አንዳንድ የትንቢት መጻሕፍት የብዙ ትንቢቶች ስብስብና ክምችት ናቸው። እነዚህ የተነጣጠሉ ትንቢቶች የተነገሩባቸው ጊዜ፥ ሁኔታና አድማጮቹም ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ። በአንድ መጽሐፍ የሚገኝ አንዱ ትንቢት በአንድ ወቅት፥ ለአንድ ወገን ተነግሮ ሌላው ደግሞ በሌላ ጊዜ፥ በሌላ ቦታና በሌላ ሁኔታ ላሉ ለሌሎች ሰዎች ተነግሮ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ ሐጌ፥ ዘካርያስ፥ ኢሳ. 13-23፥ ወዘተ። አንዳንዶቹ በግልጽ ለተለያዩ ባለ አድራሻዎች የተነገሩ ''ንግርቶች' (oracles) ናቸውና ነጣጥለን ማየት ተገቢ ነው። ትንቢቶቹ የተለያዩ ብቻ ሳይሆኑ የአጻጻፍ ስልቶቻቸው ይለያያሉ። አንዳንዶቹ በፍርድ ቤት የሚደረግ ክስና ክርክር ይመስላሉ፤ ወዮታዎች፥ የፍርድ ንግርቶች፥ የተስፋ ቃላት፥ በቅኔና ግጥም መልክ የተነገሩ ትንቢቶችም አሉባቸው። የተነገሩትና የተጻፉት ነገሮች ትንቢትነትም ከጥቂቱ በቀር ለእኛ ሳይሆን ለመጀመሪያዎቹ ተቀባዮችና ለዚያ ዘመን ነው። ካልተፈጸሙት ጥቂት በቀር ለዚህ ዘመን ሰዎች ትንቢቶቹ አሁን እንዲፈጸሙ የምንጠብቃቸው ሳይሆኑ ያለፉ፥ የተፈጸሙና ትምህርት የምንቀስምባቸው ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፋቸውና ተጠብቀው ወደ እኛ መድረሳቸው የጌታን አስጠንቃቂነት፥ ተስፋ ሰጪነት፥ እንዲሁም ቃሉን በትጋት ፈጻሚነት ያሳስቡናል። ያልተፈጸሙት ጥቂት ደግሞ ገና ወደፊት



በእርግጥ ይፈጸማሉና የተፈጸሙቱ ትንቢቶች ገና ስላልተፈጸሙት በእርሱ እንድንታመን ያደርጉናል። ጥቂት ክፍሎች፥ በከፊል ተፈጽመው በከፊል የሚቀሩ ወይም ገና የሚፈጸሙ ድርብ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው። ለምሳሌ፥ ትንቢትን፥ ሕልምንና ራእይን ከልክ በላይ የሚያጋንኑ የዘመናዊው ተሐድሶና መነቃቃት ሰባኪዎች በእጅጉ የሚጠቅሱት ጥቅስ፥ ኢዩ. 2፥28-32 በከፊል ተፈጽሞአል፤ መፈጸሙንም በሐዋ. 2፥17-21 ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ስብከቱ ከመጥቀሱ እንረዳለን። ያልተፈጸመው ክፍል ከጥቅሱ የመጨረሻ አጋማሽ ላይ የሚገኘው ነው። እንደነዚህ ሰባኪዎች አባባል 'በዚያ ወራት' የሚለው ዘመን አሁን ነው። ከሆነ እሁለተኛው አጋማሽ ላይ የሚፈጸሙት ምልክቶች ሁሉ መፈጸም እንደነበረባቸው አላስተዋሉም። ስለዚህ የነዚህን መለያ ድንበር ጠንቅቆ ማወቅ መጽሐፉን ለሚያጠኑ አስፈላጊ ነው።

ትንቢቶች ጥሩ ከመሰሉንና ተስፋ ካለባቸው ተሻምተን የራሳችን ለማድረግ እንሞክር። የመልእክቱን እውነታ ተገንዝቦ ከሕይወት ጋር ማዛመድ አንድ ነገር ነው፤ ለአይሁድም፥ ለሞዓብም፥ ለባቢሎንም፥ ለኢትዮጵያም የተነገረውን ሁሉ እንዳለ ለራስ ማድረግ ግን ትልቅ መንፈሳዊና ስነ ልቡናዊ ስሕተት ላይ ይጥላል። ኤር. 29፥11 ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚጠቀስ የተወደደ ጥቅስ ነው። ቃሉ፥ 'ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ እንጂ የክፉ ነገር አይደለም' ይላል። ቃሉን ለእኛ ብለን አንተርጉም፤ ለእኛ አይደለምና። ይህ ቃል የተነገረው በደብዳቤ ሲሆን በባቢሎን ተማርከው ለነበሩ ሰዎች ነው። ቃሉ ወይም ደብዳቤው ሳይሆን እውነቱ ግን ለእኛም ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ለእኛም የሚያስባትን አሳብ የሚያውቅ አምላክ መሆኑ ሊያስደስተንና ሊያጽናናን ይችላል፥ ይገባልም። ግን ትንቢቱ በቀጥታ ለኛ የተነገረ ቃል አይደለም። የትንቢት መጻሕፍትን ስንተረጉም፥ በተለይም ከሕይወታችን ጋር ስናገናዝብ ማስተዋል ያለብን ነገር እነዚህ ጥንትና ለሌላ ሕዝብ የተነገሩት እንደምን ከእኛና ከዘመናችን ጋር ሊገናዘቡ እንደሚችሉ ነው። እነዚህ ቃላት በቀጥታ ለእኛ የተነገሩ ባይሆኑም ልክ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ለእኛ በሚናገሩበት መልክ ጠቅላላ እውነቱ ዛሬም እንደሚሠራ አድርገን ልናይና ልንወስደው እንችላለን። ያኔ የነበረው ኃጢአት ዛሬም ያው ነው፤ ስስት፥ ጣዖት አምልኮ፥ ጥላቻ፥ እግዚአብሔርንና ሰዎችን እንዳንወድ የሚያደርጉን ነገሮች ዛሬም እንደ ዱሮው ናቸው። ስለዚህ በነጠላና በግል የኔ ብለን ባንተረጉማቸውም ጠቅላላ እውነቱን በመውሰድ ከሕይወታችን ጋር ማዛመዱ የእኛ ፈንታና ኃላፊነት ነው።

ለማጠቃለል፥ <u>የትንቢቶች መጻሕፍት ዋና ዓላማ እስራኤል እና ይሁዳ ከእግዚአብሔር ቃል አሳብ ወጥቶ ያልተወላገደ እምነትና ከዚህም እምነት የመነጨ ተግባር እንዲኖራቸው ነው። ይህ የጤና</u>

ማ እምነትና ተግባር ጉዳይ ደግሞ በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ያለ ነገር ነው። ስለዚህ ነቢያትን ስናጠና ከትንቢቱ፥ ማለትም ከተፈጸመውና ከሚፈጸመው ተስፋና ፍርድ አንጻር ይህን የጤናማ እምነትና ተግባር ነጥብ አንዘንጋ፤ ምክንያቱም፥ ከሕይወታችን ጋር ልናዛምድና ልናገናዝብ የምንችለው ይህ ነውና።

# አዲስ ኪዳን

አዲስ ኪዳን የአሮጌው ኪዳን ተቀጥላ አይደለም። አዲስ ቃል ኪዳን ነው። አዲሱ ቃል ኪዳን አሮጌውን ኪዳን ያስቀረዋል። አሮጌው ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን ለትምህርታችን እንደተጻፈ ቢኖርም እንደ ኪዳን ግን በእኛ ላይ የኪዳን ኃይልና ሥልጣን የለውም። ቀደም ሲል በብሉይ መጻሕፍት ክፍል ሕገ ኦሪትን ስንመለከት እንዳየነው አዲስ ኪዳን ከኖረ አሮጌው ኪዳን አይሠራም። አዲስ አዋጅ አሮጌውን አዋጅ ይሽረዋል። እንደገና ማስተዋል ያለብን ኪዳኑ አልተደመሰሰም፤ ነገር ግን በአዲስ ተለወጠ፤ በአዲስ ተተካ። ሕጉ ከእግዚአብሔር የመነጨ ነውና መንፈሳዊነት አለበት። ሆኖም ታማኝነትና ታዛዥነት ሳይቀሩ የአጠባበቁ ወይም የኪዳኑ ግንኙነት መንገድ ግን ተለወጠ። የሮሜ፥ የገላትያና የዕብራውያን መልእክቶች መጻሕፍት ዋና ትምህርት ይህ ነው። የቀድሞው የአጠባበቅ መንገድ በሙሴ በኩል የተሰጠውን ሕግ መጠበቅ ነበር፤ አዲሱ ግን የክርስቶስን ሕግ መፈጸም ሆነ፤ ገላ. 6፥2። ስለዚህ የአዲሱ ኪዳን ሰዎች በአሮጌው ኪዳን ሕግ ሥር አይደሉም። የሕገ ኦሪት ትእዛዛትም ሁሉ የአዲሱ ኪዳን አማኞች እንዲጠብቁአቸው የተሰጡ አይደሉም። ሆኖም ቀድመን እንዳየነው በክርስቶስ ትምህርት ጸድቀው የሚጠበቁ አሉ። ይህ አሳብ ቀደም ካለው ነጥብ ጋር የሚጋጭ አይደለም። የአሮጌው ኪዳን አንዳንድ ትምህርቶች በአዲሱም ኪዳን ውስጥ የተደገሙልን እንድንጠብቃቸው መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ምክንያቱም ከሕጉ ውስጥ ግብረ ገባዊ የሆኑቱ ዘላቂና ኀሊና ያለውን ፍጡር ሁሉ የሚመለከቱ ናቸው።

ለእስራኤል የተሰጡት የወንጀለኛ መቅጫ ደንቦች፥ ሃይማኖታዊ ወይም የአምልኮ ሥርዓቶች እና ግብረ ገባዊ ሕግጋት ናቸው። የወንጀለኛ ወይም የጥፋተኛ መቅጫ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚመለከቱት እነዚህ ሁለቱ በጣም የጠበቡና ያንን ሕዝብ ብቻና ካህናትና አገልጋዮችን ብቻ የተመለከቱ ናቸው። ግብረ ገባዊ ሕግጋቱ ግን ሰፊ አድማስ ያላቸውና በሁሉ ዘንድና ሁልጊዜ ሊጠበቁ የተገባቸው ዓይነት ናቸው። እነዚህ ግብረ ገባዊ ትእዛዛት በአዲሱም ኪዳን ውስጥ እንዲጠበቁ ተደግመዋል። እነዚህ የሚጠበቁት እዚያ የተጻፉ ቢሆኑም እዚህ ስለተደገሙ ነው። አሠርቱ ትእዛዛት፥ በተለይም ከሰንበት በቀር ዘጠኙ፥ እንዲሁም





ሕግና ነቢያት የታሰሩባቸው የተባሉት ሁለቱ እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ በግልጽ በአዲስ ኪዳንም የተጠቀሱትና የተብራሩ፥ በአዲሱ ኪዳን ሕዝብም በትጋት እንዲፈጸሙ የሚጠበቁት ናቸው። የአሮጌው ኪዳንና የአዲስ ኪዳኑ ሕዝብ ግንኙነት ይህን የሚመስል ነው። አንዳንዶች ካለማወቅ የተነሣ ክርስቶስን ከተቀበሉና ከዳኑ በኋላ ሕግን በመፈጸም የመጽደቅ ትግል ውስጥ ይገባሉ። በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የተከሰተው ችግርም ይህ ነበር። በክርስቶስ አምነው ከዳኑ በኋላ ሕግንም መጠበቅ እንዳለባቸው አንዳንድ አይሁድ ሄደው አስተማሩአቸው። ጳውሎስ ይህንን ትምህርት ልዩ ወንጌል አለው፤ ሰዎቹንም የክርስቶስን ወንጌል አጣማሚዎች ብሎአቸዋል።

ሕገ ኦሪት ወይም አሮጌው ኪዳን ለአዲሱ ኪዳን ሰዎች የተሰጠ ትእዛዝ ባይሆንም እንኳ በአፌዎት፥ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወይም ነጂነት የተጻፈ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የእግዚአብሔር ቃል ነው። ለትምህርትና ለተግሳጽ፥ ልብን ለማቅናትና በጽድቅም ላለው ምክር የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን የሚባለው ብቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ሕጉ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት ይኖሩ ዘንድ ይፈልግ እንደነበር ለማሳየትና ለትምህርትም ተጽፎልናል። የእግዚአብሔርን ባህርያት በውስጡ እናያለን፥ እንማርማለን። ብሉይን ወይም ሕገ ኦሪትን ማንም ጠብቆ መዳን አይችልም። ከአዲስ ኪዳን አንጻር ስናየው ሕጉ የተሰጠው ሰው ጠብቆት እንዲድን ሳይሆን ደካማነቱን እንዲያውቅና ወደሚያድነው አምላክ እንዲቀርብ ነው። ሕግን ፈጽሞ የጠበቀ፥ አዲሱንም ኪዳን በደሙ የመሠረተው ክርስቶስ ብቻ ነው።

በአዲሱ ኪዳን ውስጥ የአዲሱን ኪዳን መሥራች የክርስቶስን ትምህርቶችና አገልግሎት፥ የቤተ ክርስቲያንን ጅማሬና ዕድገት፥ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርቶች፥ እንዲሁም አንድ የትንቢት መጻሕፍትን እናገኛለን።

# የወንጌላት መጻሕፍት

ወንጌላት የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ታሪክ፥ በተለይም አገልግሎቱንና ትምህርቶቹን የያዙ ጽሑፎች ናቸው። ኢየሱስ የክርስትና መሥራች ብቻ ሳይሆን የሕይወታችንም መሠረት ነው። እርሱን ማወቅ ሕይወት ነው። እርሱን ለማወቅ ደግሞ ስለ እርሱ ማወቅ ያሻል፤ ስለ እርሱ ትክክለኛውን ነገር የምናውቀውም ከወንጌላት ብቻ ነው። ከዚህ የሚበልጥ ሌላ አስተማማኝ የጽሑፍ ምንጭ ከቶም የለም። ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሲታይ ወንጌላት እግዚአብሔር አስቀድሞ ያሰናዳውን የማዳን፥ የመቤዠት

ዕቅዱን ወደ አደባባይ በገሃድ ያወጣበት ታሪክ የታየባቸው ጽሑፎች ናቸው። ለሔዋን ከተነገረው ከመጀመሪያው ተስፋ ጀምሮ ስለ መሢሑ በነቢያት የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ መድረሻቸው እውን መሆኑ በወንጌላት ብቻ ነው የሚታየው።

ወንጌላት የተጻፉት በሁለት የጌታ ሐዋርያትና በሁለት ሌሎች ደቀ መዛሙርት ነው። ሁለቱ ሐዋርያት ማቴዎስና ዮሐንስ ሲሆኑ ሁለቱ ሌሎች፥ የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር መሆኑ የተመሰከረለት ማርቆስና ከጳውሎስ ጋር አብሮ ያገለገለ ሊቅ መሆኑ የታወቀለት ሉቃስ ናቸው። ወንጌላት ከአንድ ይልቅ አራት መሆናቸው አሻሚ ቢመስልም በተለያዩ ጊዜያትና ለተለያዩ ተቀባዮች የተጻፉ ናቸው። ደግሞም አንዱን ታሪክ ከተለያዩ አንጻራት በተሟላ እይታ እንድንመለከትና እንድንረዳ ይረዱናል። አንዱን ወንጌል ስናጠና በጎንዮሽ ጥናት ስልት ሌሎቹንም ወንጌላት በመመርመር ይበልጥ እንድንገነዘብም ይጠቅሙናል።

ስለ ሰዎች ኃጢአት ተሰቅሎ የሞተውንና ከሞት የተነሣውን ጌታ ለማስተዋወቅ ወንጌሉ አስፈላጊና ብቸኛ የጽሑፍ ምስክር ነው። ስለዚህም ከወንጌሉ በኋላ በነበሩት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ጽሑፎች የኢየሱስን ማንነት፥ ትምህርትና ድርጊቶች የያዙ ታሪካዊ ሰነዶች ብቻ ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍት መሆናቸውንም አውቃ ተቀበለች። <u>የወንጌላት ዋና ዓላማ ኢየሱስን አውቆ ለማመንና ለማያውቁት እርሱን ለማስተዋወቅ ነው።</u> ዋና ዓላማቸው ኢየሱስን ማሳወቅና ባወቁት በኩል ለሌሎች ማስተዋወቅ ነው። ሉቃስና ዮሐንስ የጻፉበትን ዓላማ በወንጌሎቻቸው ውስጥ አስፍረዋል። ሉቃስ፥ 'በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር. . . እርግጡን እንድታውቅ. . . ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ' ሲል፥ ዮሐንስ ደግሞ፥ 'ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል' ይላል። ስለዚህ የወንጌላት ጠቅላላ ዓላማ ሰዎች ስለ ኢየሱስ እንዲሰሙና እንዲያውቁ፥ እንዲያምኑና እንዲድኑም ነው። የተጻፈበት ቋንቋ በግሪክ መሆኑ፥ ከግሪክም በዘመኑ የሊቃውንቱ በሆነው ቋንቋ ሳይሆን በመደዴው ቋንቋ መጻፉ ጠቅላላውን ሕዝብ ለመድረስ ነው። በዘመኑ ይህ የግሪክ ቋንቋ የሮም ግዛት ዋና የመግባቢያ ልሳን ነበረ።

<u>ሌላው የወንጌላት ዓላማ ከኢየሱስ ትምህርትና ከሕይወቱ፥ ከአገልግሎቱም በክርስትና ሕይወት ልንኖርባቸው የሚገቡንን ነገሮች መቅሰም ነው።</u> ወንጌላትን ስናነብ እነዚህን ዓላማዎች ጨብጠን መሆን አለበት። በወንጌላት ውስጥ እንደምናገኘው የኢየሱስ ትምህርትና አገልግሎት ተደባልቀው ነው የምናገኘው። ትምህርቶቹ ለብቻ የሕይወት ታሪኩና አገልግሎቱ ለብቻ ሆነው አናገኝም። ይህ መደባለቅ ጠቃሚ ግንዛቤን የሚሰጠን ነገር ነው። የጳውሎስን ሕይወትና ትምህርት ያየን እንደሆነ የሕይወትና አገልግሎት ታሪኩ





በሐዋርያት ሥራ፥ ትምህርቶቹ ደግሞ በመልእክቶቹ ለየብቻ ተከማችተው እናገኛለን። ይህም የራሱ የሆነ ውበት ያለው የጽሑፍ ስልት ነው። የኢየሱስ ትምህርቶች ግን ለብቻቸው ሆነው አናገኛቸውም። ወንጌላቱ ሁለቱንም ዘርፎች ቋጥረውና ገምደው ነው የምናገኘው። ደግሞም የጻፈልን እንደ ጳውሎስ ራሱ ኢየሱስ ሳይሆን ሌሎች ናቸው። ምንም እንኳ የጻፉት ሌሎች ቢሆኑና ጌታ በሱርስጥ ወይም አራማይስጥ ቋንቋ የተናገረውን በግሪክ ቋንቋ ቢጽፉም፥ ደግሞም በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ሆነው ለተለያዩ ተነባቢዎች ወይም ተቀባዮች ቢጽፉም፥ የወንጌላቱ መመሳሰልና የይዘታቸው ቅንጅት አሁንም መለኮታዊውን እስትንፋስ ወይም አፈዎት ያመለክታል።

ወንጌላትን ስናጠና ወይም ስንፈታ በመጀመሪያ ቀጥተኛ ንግግርን ከምሳሌያዊ ንግግሮች ለይተን ማወቁ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ወንጌላት በአመዛኙ ሰሚዎች ሰምተው የዘገቧቸው የንግግር ወይም የስብከት ስብስቦች ናቸው እንጂ የተጻፉ መልእክቶች ወይም ትምህርቶች አይደሉም። በንግግር ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ስልቶች ይኖራሉ፤ ዘዬዎች፥ ፈሊጦች፥ ምሳሌዎች፥ አጋኖዎች፥ ምጸታዊ መግለጫዎች ሌሎችም ይኖራሉ። እነዚህን ሁኔታዎች ማጤኑ ይጠቅማል። ጌታ ሲያስተምር እጅግ የበዙ ምሳሌዎችን እየጠቀሰ ያስተምር ነበር። አንዳንዶቹን አድማጮቹ በቀላሉ ይረዱታል። አንዳንድ ቦታዎች ራሱ ምሳሌዎቹን ሲተረጉም በሌላ ቦታዎች ግን እንዳሉ ይተዋቸዋል። ምሳሌዎችን ራሱ ከተረጎመበት ሁኔታ አንጻር ማየትና መተርጎም ሲያስፈልግ ምሳሌ ያልሆኑት ትምህርቶቹ ግን ሊተረጎሙ አይገባም። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ክፍል እንዳየነው ምሳሌ ሉቃስ 10 ውስጥ ያለው የሳምራዊው ታሪክ እንደ ምሳሌ ተሸንሽኖ የሚተረጎም ሳይሆን የምሳሌው ዋና ትምህርት ማንንም የተቸገረ ችግረኛ መርዳት ባልንጀራን እንደራስ መውደድ መሆኑን ማሳየቱ ነው።

ሌላው ወንጌላት ሲጠኑ ስነ ጽሑፋዊውን ዐውድና ታሪካዊውን ዐውድ፥ ማለትም፥ ያ ዘመን ምን ይመስል እንደነበር መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህን ለመረዳት ታሪካዊ ሰነዶችን ወይም መርጃ ጽሑፎችን ማወቅ ወንጌላትን ለማስተማር ይረዳሉ። ታሪካዊው ዐውድ አንዳንድ ጊዜ በጽሑፉ ውስጥ ላይገኝ ይችላል። ወንጌላት በአጠቃላይ የድርጊቶችና የንግግሮች ስብስቦች በመሆናቸውና የተጻፉትም ከተፈጸሙ ከአያሌ ዓመታት በኋላ በመሆኑ ቅጽበታዊው ዳራ ወይም ታሪኩ በተፈጸመ ጊዜ የሆኑት ሁኔታዎች በአንዳንድ ቦታዎች አይገኙም። እነዚህ ነገሮች ካልተገኙ ሊተላለፍ የተፈለገው ነገር የትምህርቱ፥ የስብከቱ፥ የንግግሩ፥ ወይም የድርጊቱ ዋና አሳብ ብቻ ነው ማለት ነው። ታሪካዊ ዐውዱ ነገሩ በተፈጸመበት ሁኔታ ውስጥ ቢኖርም በጽሑፉ ውስጥ ግን ላይኖር ይችላል። ለምሳሌ በሐዋ. 20፥35 ላይ ጳውሎስ ጌታ የተናገረውን ቃል ይጠቅሳል። ይህ ቃል በተጠቀሰበት መልክ በወንጌላት ውስጥ

አይገኝም። ጳውሎስ በጠቀሰበት ስፍራ ጌታ የተናገረበት ታሪካዊ ዐውድ ባይኖርም አሳቡ ግን መቅረቡ ይታያል። የታሪካዊ ዐውዱ ያለመኖር፥ ወይም አንድ ንግግር በአንዱ ወንጌልና በሌላው በመጠኑ መለያየቱ የትምህርቱን ይዘት ከቶም አይቀንስም፥ አይለውጥምም።

የወንጌላት ትልቁ ታሪካዊ ዐውድ ወይም ትልቁ ስዕል እያንዳንዱ ወንጌላዊ ታሪኩን ሲጽፍ እንደ ትልቅ ግብ ሊያሳይ የፈለገው ነገር ነው፤ ያም፥ የክርስቶስን መሢሕነት ማሳየት ነው። ወንጌላቱ ሁሉ ወደ መስቀሉና ወደ ሞቱ የሚመሩና በትንሣኤው የተደመደሙ ናቸው። ትልቁን ስዕል ካገኘን ወንጌላትን ለመረዳት ይህ በቂ ነው። የወንጌላቱ ዓላማ የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ በዝርዝር ማቅረብ አይደለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ የሕፃንነቱና የወጣትነት ዕድሜው ዘመናት ታሪኮችም በተጻፉ ነበር። <u>እንግዲህ የወንጌላት ዓላማ የሕይወት ታሪክ ሳይሆን በሥጋ የተገለጠውን ጌታ ትምህርትና ድርጊቶች፥ ሞትና ትንሣኤውንም በማሳየት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መልእክት በጽሑፍ ማስተላለፍ ነው።</u> ለዚህ ነው ጌታ በምድር በአካለ ሥጋ ከተመላለሰባቸው ከ33 ያህል ዓመታት ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሦስት ተኩል ዓመታት ብቻ ላይ ትኩረት የተደረገው። በታሪክ ውስጥ እንደታየው ከብዙ ዘመናት በኋላ አንዳንዶች ከመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት በፊት ያለውን ታሪካዊ ክፍተት ለመሸፈን በመሻት የተፈጠሩ ታሪኮችን ጽፈዋል። እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ቢሆኑ ኖሮ ወንጌላውያኑ በጻፉአቸው ነበር፤ ባለመሆናቸውና ባለማስፈለጋቸው ግን አልተጻፉም።

የወንጌላት ዘመን የአንድ ልዩ ዘመን ድንበርም ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም መንግሥተ ሰማያት ወይም የመጨረሻው ዘመን እየተባለ የተጠራው ዘመን ጅማሬና ቀጣይ ዘመን ነው። ወንጌላትን ስናጠና ይህን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚባለውን አሳብ መረዳት ያሻናል። ይህ መንግሥተ ሰማያት ወይም የእግዚአብሔር መንግሥት የሚባለው መንግሥት በብሉይ የተተነበየው፥ በመጥምቁ ዮሐንስ ቀርባለች የተባለው፥ በጌታም በራሱ ቀርባለችና በመካከላችሁ ነች የተባለው መንግሥት አዲሱ ኪዳን እውን የሚሆንበት፥ ጽድቅ የሚፈጸምበት፥ ሰላም የሚበዛበት፥ መንፈስ የሚፈስስበት፥ የሥጋ ጉስቁልና የሚወገድበት፥ ፍጥረት ሁሉ ከመቃተት የሚያርፍበት እግዚአብሔር የሚገዛበት አዲስ ዘመን ነው። በአይሁድ ዘንድ መሢሕ እንደሚመጣና ይህ መንግሥት እንደሚጀመር በታላቅ ጉጉት ይጠበቅ ነበር። ጌታ መጣ፤ ይህንንም መንግሥት አወጀ። በዚህ መንግሥት የሚሆኑት ነገሮች ሁሉ ቅምሻ ተከሰተ፤ አጋንንት ወጡ፥ ፈውሶች ተፈጸሙ፥ ሙታንም ሳይቀር ተነሡ። ሆኖም ራሱም ጌታም በመጨረሻ ተሰቅሎ ተገደለ። በአይሁድ የሚጠበቀው መሢህ እንዲህ መሆን አልነበረበትም። በዚህ ግን አላበቃም ሞትን ረትቶ ተነሣ።





በአይሁድ የተናፈቀው ምድራዊ መንግሥት ግን አሁንም አልተጨበጠም።

ከትንሣኤው በኋላ ሐዋርያትም በሐዋ. 1፥6 እንደተጻፈው ይህን መንግሥት ጠብቀውና ጠይቀው ነበር። ጌታም ወደ ሰማይ በማረግ በላይኛው ዙፋን ተቀመጠና መንፈስ ቅዱስን ላከ እንጂ በምድራዊ ዙፋን አልተቀመጠም። በቀጣዮቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደምናየው ሐዋርያትም ምዕመናንም የእግዚአብሔር መንግሥት መጀመሩን፥ ይህም ጅማሬ የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑን እንጂ ፍጻሜው አለመሆኑን እንደተገነዘቡ እንረዳለን። የመጨረሻው ዘመን ወይም የእግዚአብሔር መንግሥት ተጀምሮአል፤ ፍጹም የሆነ አገዛዙ በምድር የሚሆንበት የመጨረሻ ዘመን ግን አሁንም ገና ወደፊት ነው። ሰማይና ምድር ካለፉ በኋላ በአዲስ ሰማይና ምድር የሚሆነው፥ ዘላለማዊ መንግሥቱም ከዚያ በኋላ የሚሆን ነው። በጌታ መምጣት፥ ሞትና ትንሣኤ የተጀመረው መንግሥት ውስጥ አሁን ገብተን እንገኛለን። ያመንንበት እኛ ቤዛነትና ሕይወት፥ ሰላምና ጽድቅ፥ ጸጋና ብዙም በረከት ሆኖልናል። ነገር ግን ገና ዳግም ሲመጣ የተተነበዩት መንፈሳዊ፥ ሥጋዊ፥ ምድራዊ በረከቶች ሁሉ ምንም ሳይጓደሉ ይፈጸማሉ። እነዚህ ሁለቱም የአንዱ የእግዚአብሔር መንግሥት ሁለት ደረጃዎች ናቸው። እነዚህን ደረጃዎች መረዳት የአንዱን ባህርይ ከሌላው ጋር እንዳናጋጭ ይረዳናል። ለምሳሌ፥ አሁን በልባችን ሰላም አለ። በምድራችን ግን የለም፤ ቢኖርም ያለው አንጻራዊ ሰላም ነው። በዳግም ምጽአቱና በሺ ዓመቱ መንግሥት ግን በምድርም ሰላም እንደ ወንዝ ይፈስሳል። ሌላ ምሳሌ፥ አሁን እግዚአብሔር በጤና ይባርከናል፤ ሆኖም ከሕመምና በሽታ ነጻ ላንሆን እንችላለን። በመጪው መንግሥቱ ግን ሕመምና ደዌ ከቶ አይኖርም። በፍጻሜው መንግሥቱ እንዲያውም ሞትም ከቶ አይኖርም። እንግዲህ የመንግሥቱን የአንዱን ገጽታ ወይም ደረጃ በረከት ከሌላው ጋር አጋጭተን አሁን እንበልጽግ፥ አሁን ከሕመም ነጻ እንሁን፥ አሁን በምድር ሰላም ይሁን፥ አሁን ሞት ይሙት ማለት አይኖርብንም።

ወንጌላት የዋናው ባለ ታሪክ የኢየሱስ ታሪክ ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው መልእክት የተላለፈበት ጽሑፍም ነው። ስለዚህ ወንጌላውያኑ ወንጌሎቹን ሲጽፉ የተወሰኑ ታሪኮችን እንዲመርጡና ለወንጌሉ የቅርብና የሩቅ ተቀባዮች ተገቢ መረዳትን በሚሰጡበት ሁኔታ ተመቻችተው እንዲጻፉ አድርጎአል። ዮሐንስ በ21፥25 ላይ ስለ ታሪኩ ስፋትና ጥቂት ታሪኮች ብቻ ስለመመረጣቸው ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ የወንጌላቱ ጸሐፊዎች ምንን ወስዶ ምንን መተው እንዳለባቸውም መቆጣጠሩን ቀደም ካሉት ክፍሎች ደጋግመን አይተናል። ወንጌላውያኑ ታሪኮቹን ሲሰበስቡ ወይም ሲመርጡ የተለያዩ ምክንያቶች እንደነበሩአቸው መረዳት አያስቸግርም። እንዳየነው ዮሐንስ እንዲህ ማድረጉ ተጽፎአል። ዮሐንስ ከሌሎቹ ያነሰ ጥቂት ታሪክ መርጦ በተወሰኑት

ላይ የተለየ ትኩረት ማድረጉ በግልጽ ይታያል። ዓላማውም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ወይም መሢሑ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንድናምንና አምነንም ሕይወት እንዲሆንልን ነው። ለዚህም ይመስላል ከሌሎቹ ከሦስቱ ወንጌላት ይልቅ ከገሊላ አብልጦ በይሁዳና በኢየሩሳሌም አገልግሎቱ ላይ ያተኮረው። ይህ የጸሐፊዎቹ የጽሑፍ ይዘት መረጣ ወይም የታሪክ ለቀማ የጸሐፊዎቹን ዓላማ የተከተለ ነው። የጻፉበት ዓላማ የጻፉአቸውን ታሪኮች እንዲመርጡ አድርገዋቸዋል። ይህ ከጽሑፍ ስልት አኳያ ሲታይ ሲሆን በምርጫውም ሆነ በጽሑፉ ሂደት ውስጥ ግን ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ይሆን ዘንድ የእርሱ መንፈስ አለበትና መንፈስ ቅዱስ እንደ ሌሎቹ ጽሑፎች ሁሉ መሥራቱ መዘንጋት የለብንም።

ወንጌላትን ስናጠና የጌታን አገልግሎትና ትምህርት፥ ደግሞም ለምን ዓላማ መምጣቱን እንደ ትልቁ ስዕል በማየት በውስጡ የተደረጉትን ነገሮችና የተነገሩትን ትምህርቶች በነጠላ ማየት አለብን። ቀደም ሲል እንዳየነው በአንዳንድ ቦታዎች ታሪካዊ ዐውዱ ባይኖርም ትልቁን ዓላማ ጨምሮ ስነ ጽሑፋዊው ዐውድ ግን አለ። አንድን ነጠላ ታሪክ ከወንጌሉ ውስጥ ወስደን ስናጠና ማየት ያለብን ሦስት ዋና ዋና ነገሮች፥ ጠቅላላው ስዕል፥ ማለትም ወንጌሉ በሙሉ፥ ታሪካዊ ዐውድ ከኖረ ታሪካዊ ዐውዱ፥ እንዲሁም ታሪኩ የተጻፈባቸው ሌሎች ወንጌላት ወይም ያንን ትምህርት የሚመስሉ ሌሎች የወንጌሉ ክፍሎች ናቸው። ታሪኩ በሌላ ወንጌል ውስጥ መጻፉ ይበልጥ ያብራራዋል። በክፍሉ መግቢያ ላይ እንደተመለከትነው አራት ወንጌላት መጻፋቸው አንድም ለዚህ ነው። የአንዱ የእይታ ገጽታ ከሌላው ይለያልና ታሪኩን ግልጥና ሙሉ ያደርገዋል። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ወንጌሎች በይበልጥ መቀራረብ አላቸውና ብዙ ተመሳሳይ ነገሮች ይነበቡባቸዋል። ይህ የጎን ለጎን የወንጌላት ታሪክ እይታ ነው።

ከጎን ለጎን እይታው በተጨማሪ የዙሪያ እይታም ተፈላጊ ነው። ይህ ሰፊና ጠባብ ስነ ጽሑፋዊ ዐውዱን፥ ታሪካዊ ዳራውን፥ እንዲሁም ባለታሪኩን ማየት ናቸው። ስለ ስነ ጽሑፋዊ ዐውድ ደጋግመን ስላየን እዚህም መድገም አያሻም። ሆኖም ግን በወንጌል ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ቀነጫጭቦ ሳይሆን አንዱን ወጥ ታሪክ እንዳለ መውሰድ ጤናማ አወሳሰድ ነው። ታሪካዊ ዳራውም ታሪኩ እንዲነገር ወይም እንዲጻፍ ያደረጉትን ነገሮች ይይዛል። ባለ ታሪክ ሲባል ደግሞ የታሪኩ ዋና ባህርይ ነው። የወንጌላት ዋና ባለ ታሪክ ኢየሱስ ነው። ሲናገር፥ ሲያደርግና ሲሆን የምናየው እርሱን ነው። ይሁን እንጂ ወንጌላት የተጻፉት የኢየሱስን ታሪክ እንደ ታሪክ ጽፎ ለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ነውና እኛ እንድናምንበት፥ እንድንማርበትና እንድንኖርበት የኢየሱስን ሕይወት፥ ትምህርትና ሥራ ለማሳየት ነው። ትምህርትና ሥራውን ብቻ ሳይሆን የምትክነት ሞቱንና ትንሣኤውንም ለመግለጥ ነው። ከወንጌላቱ ትኩረት እንደምናገኘው የመጣበት ዋና





ዓላማ ተአምራትን ለመሥራት ሳይሆን ለቤዛዊ ሞትና ሞትን ድል ለመንሣት ነው። ይህ የወንጌላት አጠቃላይ ግብ ስለሆነ ይህ ሳይዘነጋ ነው ወደ ነጠላ ታሪኮች ውስጥ መግባትና ማጥናት ያለብን።

ወንጌላትን ስናነብ፥ ስንፈታና ስናገናዝብ ታሪኩ የተነገረበት ዘመን ብሉይ ኪዳን መሆኑንም አንዘንጋ። ምንም እንኳ መጻሕፍቱ በአዲስ ኪዳን የመጻሕፍት ስብስብ ውስጥ ቢሆኑም ዘመኑ ግን ገና የሕግና የአሮጌው ኪዳን ዘመን መሆኑ ሊስተዋል ይገባል። አንዳንዶች ይህን አሳብ ያለልክ በመለጠጥና ከአሳቡ በመራቅ ኢየሱስ የሰጣቸው ትእዛዛትም ራሳቸው በሕግ ዘመን የተሰጡ ሕግጋት ናቸው፤ ሕግ ደግሞ አያድንም ጸጋ እንጂ፤ ስለዚህም መጠበቅ የለብንም ወደሚል ድምዳሜ የመጡ አሉ። ይህ በእርግጥ ከእውነቱ መራቅ ነው። ትእዛዛቱን ስናስብ አጽንተን ማስተዋል ያለብን ነገር ግን እነዚህ የክርስቶስ ትእዛዛት ጠብቀናቸው እንድንድን የተሰጡን አለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን በጸጋው ከዳንን በኋላ መታዘዛችን የመዳናችን ምልክቶች መሆናቸውንም ነው። በእርግጥ የምንድነው በጸጋው እርሱን በማመን ብቻ ነው እንጂ በማናቸውም ዓይነት የሕግ ሥራ አይደለም። ነገር ግን ትምህርቶቹ እርሱን ካመንን በኋላ ወይም ክርስቲያን ከሆንን በኋላ እንደምን መመላለስ እንዳለብን የሚያስተምሩ ትምህርቶች ናቸው። የክርስቶስ ትእዛዛት የአዲስ ሕይወት መገለጫዎች ናቸው እንጂ እንደ ሙሴ ሕግ ያሉ አይደሉምና እንኖርባቸው ዘንድ ይጠበቅብናል።

# የአዲስ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍ

ይህ የታሪክ መጽሐፍ የሐዋርያት ሥራ ነው። ወንጌላትም የአዲስ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ናቸውና ሌላ የታሪክ መጽሐፍ በተጨማሪ ከመጻፍ ይልቅ የአተረጓጎም ስልቶቹን ከወንጌላት ጋር ወይም ከብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ጋር ማያያዙ ይቀልል ነበር። ግን ይህ መጽሐፍ የታሪክ መጽሐፍ ቢሆንም፥ በተለይም የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ምዕራፎች በአንዳንድ ዘመናዊ የመነቃቃትና ተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ዘንድ፥ እንደ ታሪክ መጽሐፍ ከመታየት ይልቅ እንደ ሕግ ወይም እንደ ደንብ ተደርገው የሚወሰዱ በመሆናቸው የተገባውን የስነ አፈታት ስፍራ ለብቻው ማየቱ አስፈላጊ ነው። ይህንን መጽሐፍ በተገቢው ሁኔታ ያለመመልከት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚገልጠው ባለፉት ብዙ ዘመናት በርካታ አሻሚ ተግባሮች እንዲከሰቱ አድርጎአል። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅንና በልሳናት መናገርን አንድ ማድረግ፥ የሕፃናት ጥምቀትን፥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን፥ ንብረትን እየሸጡ በማህበር መኖርን፥ ወዘተ የመሰሉትን አላግባብ በመፍታት ሲያዛቡ ይገኛሉ። ከዚህ ሌላም የተለያዩ አዳዲስና እንግዳ ትምህርቶች

እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትን ያለ ወግ የሸነሸኑ ትምህርቶች ጅማሬ 'በሐዋርያት ሥራ ተጽፎአል' በሚል መነሻና ማሳበቢያ ነው።

የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው። ቀድሞ እንደተነገረውም የወንጌሉ መስፋትና የክርስቲያኖችም ከኢየሩሳሌም እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቹ የመሆናቸው ታሪክ ነው። ብዙዎች ይህን መጽሐፍ ከተለያየ ግፊት አንጻር ያጠኑታል። አንዳንዶች ለታሪክ ፍለጋ፥ ሌሎች የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን እንደ ናሙና በመውሰድ ዛሬም እንደዚያ ለመሆንና ለማድረግ፥ ሌሎችም ጠንካራ የትምህርትና የተግባራዊ አስተምህሮ መሠረት ለመፈለግ፥ ሌሎችም ከአንድ ጥቅስ ወይም አንቀጽ ተስፈንጥሮ በመነሣት ልምምዳዊ እምነትን ለማስፋፋት፥ ሌሎችም ለሌላ ግብ ያጠኑታል። የሐዋርያት ሥራን በተመለከተ ትክክለኛው ጥናት ጠቅላላ መጽሐፉን ከታሪካዊ ይዘታው ጋር መመልከት ነው። መጽሐፉን ሉቃስ ሲጽፈው በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ከወንጌሉ ቀጥሎ ያለውን ታሪክ እየዘገበ መሆኑን እንዘንጋ። በመግቢያው ላይ ይህን ነው የገለጠው።

ማናቸውም የታሪክ ጽሑፍ ሁለት ዋና ዋና ግቦች አሉት፤ የመጀመሪያው ያለፈውን፥ የሆነውን ነገር መዘገብ ነው። ይህ ዘገባ የራሱ የሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላሉ። ሁለተኛው ደግሞ ያንን ያለፈውንና የሆነውን እውነት በማሳወቅ ግብረ ገባዊ ወይም መንፈሳዊ እውነትን ማስተላለፍ ነው። የሐዋርያት ሥራ ሁለቱንም ያጣምራል። ይህ ሁለተኛው አሳብ በተለይ ከታሪኮቹ ውስጥ የቱን አንስቶ የቱን ጥሎ መሥራትን ይበልጥ የሚነካ አሳብ ነው። መጽሐፉ በአጠቃላይ ከሠላሳ ዓመታት በላይ የሆነ የቤተ ክርስቲያንና የሐዋርያትን ታሪክ ቢይዝም እንደ ዘመኑ ብዛት ሰፊ አይደለም። የሐዋርያትን ሁሉ ሥራም የያዘ አይደለም። በወንጌላት አጻጻፍ ላይ መረጣ የሚለውን አሳብ እንዳየነው እዚህም ተመሳሳይ ነገር ነው የተደረገው። ወንጌላት በኢየሱስ ዜና ሕይወት ላይ ሳይሆን የተመረጡ ትምህርቶቹና ሥራዎቹ ላይ እንዳተኩሩ ይህም እንዲሁ ነው። እነዚህ የተመረጡ ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተለቀሙ ናቸውና ለእምነትም ለክርስቲያናዊ ኑሮም በቂያችን ናቸው።

ዮሐንስ በመደምደሚያው ላይ ወንጌሉን ለምን እንደጻፈ እንዳስቀመጠልን ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ለምን እንደጻፈልን አልተናገረም። ከመጀመሪያው መጽሐፍ ግን ቀጣዩ መሆኑ ተጽፎአል። ስለዚህ ይህ የቀደመው ታሪክ ቀጣይ መሆኑን ከዚህ እንረዳለን። ምንም እንኳ ቃሉ በሰፊ ትርጉሙ የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ ቢወሰድም የተጻፈለት ቴዎፍሎስም ማን መሆኑ የታወቀ አይደለም። የሐዋርያት ሥራ የሉቃስ ወንጌል ተከታይ ከሆነ ደግሞ በሉቃ. 1፥1-4 ያለው የሉቃስ ወንጌል የጽሑፍ ዓላማ ለሐዋርያት ሥራም ይሆናል ሊባል ይቻላል። አንዳንድ ተርጓሚዎች





የሐዋርያት ሥራ የተጻፈው የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ለተከታዮቹ ዘመናት አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ ወይም ናሙና ለማድረግና ፈለጓን እንድንከተል ነው ይላሉ። እንዲህ ከሆነ የትኛዋ መሆንዋ አሻሚ ይሆናል፤ በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተጠቅሰዋልና። ይህ ካልሆነም የሁሉንም ጥርቅም ወስዶ በማንኛውም ዘመን፥ በየትኛውም ቦታ፥ በምንም ዓይነት ሁኔታ ባለች ቤተ ክርስቲያን መተግበር ሊኖርበት ነው። የመጀመሪያዋ በኢየሩሳሌም የነበረችው ከሆነች ቀጥሎ የታዩትም የመጀመሪያዋን ፈለግ መከተል ግዴታ ሊሆንባቸው ይሆናል። ስለዚህ ነው የሐዋርያት ሥራን በመጠኑ ለብቻ መመልከት አስፈላጊ የሚሆነው።

መጽሐፉ በአካሄዱ አንዱን ታሪክ ከሌላው ለመለየት የተሠሩለት ድንበሮች ቢኖሩም ትክክለኛው የዚህ መጽሐፍ አጠናን መጽሐፉን በሙሉ በአንድ ጊዜ፥ በአንድ ንባብ ጨርሶ አንብቦ ደግሞ ጉልህ ነገሮችን በማጤን እንደገና ማንበብና ከዚያ ንዑሳን ክፍሎችን ለይቶ ማጥናት ነው። ንባቡ የመጽሐፉን ጠቅላላ አሳብ ያሳየናል። ዳግም ንባቡ ዋና ዋና እና የተደጋገሙ ሰዎችን፥ ቦታዎችን፥ ሁኔታዎችን፥ ድርጊቶችን እንድናስተውል ይረዳናል። ቀደም ባሉት ክፍሎች እንዳየነው ትልቁን ስዕል ካየን በውስጡ ያሉትን ነገሮች ለመረዳት ያላየነውን ያህል አንቸገርም። የሐዋርያት ሥራ የሐዋርያት ታሪክ አይደለም። ከቀደምት ሐዋርያት በስፋት የተጠቀሰው ጴጥሮስ ብቻ ነው። ያዕቆብ አሟሟቱ ሲጠቀስ ዮሐንስም ጥቂት ተጠቅሶአል። የቀሩት እንዲያውም በመጀመሪያው ምዕራፍ ብቻ ከመጻፋቸው በቀር አልተጠቀሱም። ጴጥሮስ ደብዝዞ ከጠፋ በኋላ የጳውሎስ አገልግሎትና የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደምቆ መታየት ጀመረ። ይህ እስከ መጨረሻው ድረስ የሄደው ታሪክ ነው። ስለዚህ ታሪኩ የሐዋርያት ሥራ ቢባልም የሐዋርያት ታሪክ አይደለም። በጉልህ የታዩት የሁለቱ፥ የጴጥሮስና የጳውሎስ ዜና ሕይወትም አይደለም።

የሐዋርያት ሥራን በተበጁለት ድንበሮች ካየነው በሁለት አቅጣጫ ልንመለከተው እንችላለን። አንደኛው አከፋፈል የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ 12 ያለው በጴጥሮስና በአይሁድ አማኞች ላይ የሚያተኩረው ሆኖ ሁለተኛው ደግሞ ከ13 እስከ 28 ያለው በጳውሎስና በአይሁድና አሕዛብ አማኞች ላይ የሚያተኩረው ክፍል ነው። ሁለተኛው አከፋፈል ደግሞ በወንጌል ስርጭት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም፥ ኢየሩሳሌም፥ 1 እስከ 7፤ ይሁዳ፥ 8 እስከ 10፤ የምድር ዳርቻ፥ ከ11 እስከ 28 ናቸው። እንዲያውም በመጽሐፉ ውስጥ ከእንዲህ ያለው ሦስትዮሽ ክፍፍል ይልቅ ቀጥተኛ የሆነ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ወደ ሮም የተጓዘ ታሪክን ማየቱ ይቀልላል። በሁለቱም አከፋፈል የምንመለከተው የቤተ ክርስቲያንን በአገልግሎትም በመልክዓ ምድርም ማደግና መስፋት ነው። ታሪኩ የሚቋጨውም በዘመኑ የዓለም ዋና መዲና በሮም ወንጌሉ ለአሕዛብ ሲሰበክ በማሳየት መሆኑ ቤተ ክርስቲያን

<u>ከአንድ ወገን፥ ማለትም፥ ከአይሁድ ወደ አሕዛብ አቀፍና ዓለም አቀፍ ይዞታ ማደጓን ነው።</u>

ሉቃስ ይህን የወንጌል መስፋት እንደ ዓላማ ጨብጦ የተነሣ ይመስላል። ይሁን እንጂ የዚህንም ዝርዝር፥ ማለትም፥ አብያተ ክርስቲያናትንና ተግባራቸውን በዝርዝር ሲጽፍልን አናገኝም። በሌላ ክፍል የተጠቀሱ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በሐዋርያት ሥራ እንዲያውም ሳይጻፉ ቀርተዋል። ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና አመራርም አልጻፈም። ይህ የሚያሳየው እነዚህ ነገሮች የጽሑፉ ግቦች አለመሆናቸውን ነው። ደኅንነትንና ክርስቲያናዊ ሕይወትን በተመለከተም ሉቃስ አንድና አንድ ዓይነት ልምምድን ብቻ አላቀረበም። አንዳንዶች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ በልሳኖች ተናገሩ፤ ሌሎች ደግሞ አልተናገሩም። አንዳንዶች ካመኑ በኋላ ሁሉን እየሸጡ በአንድነት ኖሩ፤ ሌሎች ደግሞ አልኖሩም። እንዲያውም በአንድ ላይ የኖሩትም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተበታተኑ። በአንዳንድ ቦታ የታሰሩ ተፈቱ፥ በሌላ ቦታ ደግሞ ተይዘው የታሰሩ ተገደሉ እንጂ አልተፈቱም። አንዱ ተነጥቆ ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ሲወሰድ እናያለን፤ ሌላው ደግሞ ይግኣዝባት የነበረች መርከብ ተሰብራ ስትሰጥም እርሱና አብረውት የነበሩ በጭንቅ ሲተርፉ እናነብባለን። ጸሐፊው አንዱንም ነጥብ እንደ ዋናና ብቸኛ ልምምድ ወይም የአገልግሎት ስልት ወይም የአስተዳደር ዘይቤ ወይም የሕይወት ናሙና አድርጎ ሲያቀርብ አይታይም።

በአጠቃላይ ግን እንደ ዓይነተኛ ናሙና አድርጎ የሚያቀርበው ነገር አለ ብለን ልንወስድ የምንችለው እውነት አለ። ያም፥ የወንጌሉ ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር፥ ግለ ሰቦችና ቤተ ሰቦችን፥ በአንዳንድ ስፍራም ማኅበረ ሰቦችንም ጭምር አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በመለወጥ እንደ ቋያ እሳት መስፋፋቱ፥ ቤተ ክርስቲያንም የዚህ መስፋፋት ዋና መሳሪያና መረማመጃ መሆኗ ነው። ቤተ ክርስቲያን የወንጌል አስፋፊ መሆንዋ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምትደገፍ መሆንዋ፥ በተለወጡ ሰዎች መሞላትዋ፥ እነዚህ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሁነኛ ናሙና ተደርገው ሊወሰዱ የተገባቸው እውነቶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሂደት ውስጥ ውጪያዊ ተጽዕኖና ስደትም፥ ውስጣዊ ጠባብነትና መከፋፈልም ሳያግዱአት በፈጣን እርምጃ ነበር ያደገችው። እንደ ዓይነት ከተወሰደ እንዲህ ዓይነቱ ዕድገት ሊወሰድ ይገባዋል። ይህ ትልቅ ስዕል ተይዞ ነው ወደ ነጠላ ታሪኮች መወረድ ያለበት። በሐዋርያት ሥራ የምናያት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ስለሆነች ብቻ እንደ ናሙና ትወሰዳለች ማለት አይደለም። የመጀመሪያዋ እንዲሁም በዚያ ዘመን የተተከሉት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቀደምት እንደመሆናቸው መጠን ግን ፈር ቀዳጆች መሆናቸውን አንዘንጋ። ቤተ ክርስቲያን በበርካታ ገጽታዋ ምን መምሰል እንዳለባት በቀጣይ መልእክቶች ውስጥ የምናገኘው ነገር ባይኖር ኖሮ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናገኘው ታሪክ





ብቻውን መመሪያ ይሆንልን ዘንድ ይገባ ነበር። ነገር ግን ገጽታውን ሙሉ የሚያደርጉ ሌሎች ቅዱሳት ጽሑፎች መኖራቸው ለመጽሐፉ ተገቢውን ስፍራ ይሰጠዋል።

በመጽሐፉ ውስጥ የተጻፈውን ታሪክ አንዳንዶች እንዳለ እንደሚደገም ተደጋጋሚ ነገር አድርገው ይፈቱታል። እንዲህ ሲያደርጉ ግን ብዙዎቹ መርጠው የተወሰኑትን እንጂ ሁሉንም አይደለም። አንዱን መርጠው ሌላውን ለመተዋቸው ደግሞ ምክንያት የላቸውም። እንዲህ ያለውን አፈታት ከማቀፋችን በፊት መጠየቅ ያለብን ነገር፥ 'ነገሩ በግልጽ በቃሉ ውስጥ እንድንከተለው ወይም እንድናደርገው ተነግሮናል?' የሚል ነው። እንዲህ ከሆነ ሳናወላውል መከተል አለብን፤ ያለዚያ ግን እንደ ታሪክ የተጻፈውን ነገር ሁሉ እንደ ትእዛዝ ከተከተልነው ወደ ውስብስብና ግራ አጋቢ ልምምድ ውስጥ እንገባለን። የተፈጸመ ታሪክ ማለት የሚደጋገም ልምምድ ማለት አይደለም። እንዲህ የሚፈቱትም የተጻፈውን ታሪክ እንደ ትምህርት አድርገው በመውሰድ፥ 'ቃሉ እንዲህ ያስተምራል' በማለት የሚያስተምረውን ሳይሆን የተጻፈውን ታሪክ ይጠቅሳሉ። የተፈጸመ ታሪክ ስለተዘገበ ብቻ፥ ወይም ለኛ መልካም መስሎ ስለታየን ብቻ እንደ ዋና ትምህርት ወይም አስተምህሮ መወሰድ እንደሌለበት የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍትን ስንመለከት አይተናል።

ይህን ማለት እነዚህ ታሪኮች ጨርሶውኑ እንደ ትምህርት አይወሰዱም ማለት አይደለም። ነገር ግን እንደተፈጸሙ የተዘገቡ ታሪኮች ናቸውና እንደ ሥነ መለኮታዊ መሠረት ወይም እንደ ዋና አስተምህሮ ተደርገው አይወሰዱም። መሪ ለመምረጥ ዕጣ መጣል አለብን፤ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል እንዲወርድ አሥር ቀናት መጠበቅ አለብን፤ ንብረታችንን ሸጠን በማኅበር መኖር አለብን፤ ወዘተ ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ እነዚህና እነርሱን የመሰሉት ነገሮች በራሳቸው የሚያስተምሩን ነገር የለም ማለት አይደለም። አለ። ማናቸውም የታሪክ ጽሑፎች እንደሚያስተምሩን ሁሉ እነዚህም ታሪኮች ያስተምሩናል። ሆኖም ሁሉንም ነገሮች በሁሉ ቦታ ያሉ አማኞች በሁሉም ዘመን ሊያደርጉት ይገባል የሚሰኙ ትእዛዛት አይደሉም። <u>በታሪኩ ውስጥ ታሪኮቹ ቢጻፉም በሁሉ ዘመን በሁሉ ቦታ ያሉ አማኞች ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች በሌላ ቦታ በግልጽ የተሰጡ ትምህርቶችን ማየቱ አስፈላጊ ነው።</u> ለምሳሌ፥ በሐዋርያት ሥራ ሰዎች በልሳናት የተናገሩበት ታሪኮች ተጽፈዋል። ስለ ልሳናት ያለን ትምህርት በዚህ መጽሐፍ ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ወደ ሁከትና ትርምስ ልንገባ እንችላለን። ምክንያቱም በነዚህ ቦታዎች የተፈጸሙት ክስተቶች ብቻ ናቸው የተጻፉት እንጂ ሥርዓቱ አልተነገረም። ይህ ጸጋ በጉባኤ ውስጥ እንደምን መደረግ እንዳለበት ለመረዳት በሌላ፥ ይህ ትምህርት በግልጽና እንደ ታሪክ ሳይሆን እንደ ትምህርት በተጻፈበት ቦታ ምን እንደተባለ አንብበን መረዳት አለብን፤ ይህን በ1ቆሮ. 12 እስከ